## መግቢያ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 እና መ/ቤቱን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 186/2003 መሠረት፣ በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለመደበኛ ተግባራትና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን፤ የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው ሕግ፣ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን፣ ከምዝበራና ብክነት መጠበቁን ለማረጋገጥ የክልሉን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ የቆዳ ስፋት፣ የአወቃቀር እርከንና የሴክተር አደረጃጀት፣ ለየመ/ቤቱ እንዲሁም ለመ/ቤታችን የተመደበውን በጀት፣ ያለውን የሰው ኃይል እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመከተል ያከናወናቸውን ተግባራት ያካተተ አጠቃላይ ዘገባ በዚህ ጥራዝ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት የተጠቃለለው ውጤት እንደሚያመለክተው፡-

1. መ/ቤቱ ከጥር 2007 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ/ም ባሉት 12 ወራት የ259 መ/ቤቶችን የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ249 (96.13%) አከናውኗል፡፡ የሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት ውጤት እና የመ/ቤቱ አጠቃላይ የ2008 በጀት ዓመት የ11 ወራት የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ ሪፖርት ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡
2. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረገ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 70 (28.11%)፣በዞን 9 (3.62%)፤በከተማ አስተዳደሮች 31 (12.45%) ቀሪዎች 139 (55.82%)፤በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ካሉት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው 442 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 56.33% የደረሰ ሲሆን የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ ደግሞ አጠቃላይ ኦዲት የተደረገ መ/ቤቶች የበጀት ወጪ ብር 17,130,995,857.81 በመሆኑ በ2007 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው ብር 21,526,627,543 አኳያ ሲታይ 79.6% የኦዲት ሽፋን ላይ እንደተደረሰ መረጃው ያሳያል፡፡
3. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል::
4. የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሠሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው::
5. የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች ከጥሬ ገንዘብ፣ከገቢ፣ከተሰብሳቢ፣ከወጪ፤ከተከፋይ፣ከበጀት፣ከሂሣብ ሪፖርቶችና ከንብረት አስተዳደር ኦዲት የተገኙ ሲሆኑ በሪፖርቱ ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

   በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 24,202,262.19 የገንዘብ ጉድለትና ማጭበርበር የተከሰተ እንዲሁም ለግል ጥቅም የዋለ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ከፍተኛ ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች በቅደም ተከተል ከከፍተኛው በመጀመር እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

- የደብረ ብርሃን እንጨት ማቀነባበሪያ ኃ/የተ/የግል ማህበር ብር 15,048,802.55፤ **በላይ አርማጭሆ ወረዳ የትክል ድንጋይ መሪ መዘጋጃ ቤት** ብር 2,500,000.00፣የከሚሴ መምህራን ትምህርት ኮላጅ ብር

1,693,403.72 ፣ **የአብክም ገጠር መንገድ ባለስልጣን** ብር 1,089,120.74 ፣**ደራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰማዕከል** ብር 937,201.77፣ **የደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር 785,283.65**፣ ደብረ ማርቆስ ከተማ ውሃ ፍሳሽ አግልግሎት ጽ/ቤት ብር 479,759.20፣ አልቡኮ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ብር 366,825.96፣ **የወረባቦ ወረዳ ገጠር መንገድ ልማት ጽ/ቤት** ብር 317.899.95፣ ደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር 208,567.15፣ የቃሉ ወረዳ ንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ብር 195,630.00፣ **የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ** ብር 179,372.50፣ ደልጊ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ብር 173,027.00 ፣ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 40,235.17፣ቦረና አጠ/ደ/መስናዶ 2ኛ ደ/ት/ቤት ብር 19,146.00 ፣የኮምቦልቻ ቁ.2 አጠ/1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 10,957.45፣ ሲርባ መነብኮ አጠ/1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 17,876.64 ፣ወረባቦ ወረዳ ገጠር መንገድ ልማት ጽ/ቤት ብር 34,416.30፣ በሳይንት ወረዳ የአምባ ፈሪት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 42,922.11፣የሳህላ ሰየምት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ብር 79,528.46 ፣ አንዳሳ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር 35,500.00፣አዲአርቃይ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 27,290.73፣ የቦረና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ብር 10,643.28 ፣**የእንጅባራ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ** ብር 17,753.26 ፣**የረቡዕ ገበያ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት** ብር 13,200፣ **ዳባት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ** ብር 5,000.00፣**የጉባላፍቶ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት** ብር 19,395.25 ፣ቦረና አጠ/ደ/መስናዶ 2ኛ ደ/ት/ቤት ብር 19,146.00 የትምህርት ቤቱ የንብረት ሰራተኛ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣ በሳይንት ወረዳ የአምባ ፈሪት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የንብረት ሰራተኛ /ፋርማሲ ቴክኒሽያን/የሆኑት ያንቀሳቀሱት የመድሃኒት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት ብር 42,922.11 ፣ ደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር 208,567.15 ንብረት ክፍል ሰራተኛው ከ2000 ዓ.ም እስከ 30/10/2007 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣ በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ የተገኘ ሲሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የመንግስት መ/ቤቶች ከብር 10,000.00 በላይ ጉድለት ወይም ማጭበርበር በመፈጸም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው:

6. በዚህ አጠቃላይ ዘገባ ለየመ/ቤቱ ከተላከው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች ዝርዝር ተለቅመው የተጠቃለሉ ግኝቶች እንዲሁም ከ2003 እስከ 2007 ባሉት 5 ዓመታት በተከናወነ ኦዲትና በተዘጋጁት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት አዝማሚያውን ለማሳየት የዋና ዋና ግኝቶች አማካይ ውጤት በግራፍ ተደግፎ ቀርቧል፡፡የዚህ ሪፖርት ዋና ዓላማ የክልሉ ምክር ቤት የበጀትና መንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የርዕሰ መስተዳድርና ክልል መስተዳድር ም/ቤት ጽ/ቤትና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶችን ግኝቶች በመገምገም የፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደሩን አጠቃላይ ሁኔታዎች ለማሻሻል ለሚደረጉ ውሳኔዎች እንዲጠቀሙበትና ተጠያቂነትንም ለማጠናከር በማሰብ የቀረበ ነው::

7. የሪፖርቱ አቀራረብ የ2007 በጀት ዓመት ሂሣብ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ውጤት እና የመ/ቤቱን የ11 ወር የሥራ እንቅስቃሴ፤ያለፉት አምስት ዓመታት አፈጻጸም አዝማሚያ ትንተና ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየት በቅደም ተከተል ከምዕራፍ 1-3 በማካተት ሲሆን ለሪፖርቱ ደጋፊ አባሪዎች 128 ገጽ በሪፖርቱ መጨረሻ ተያይዘዋል፡፡

# ምዕራፍ -አንድ

1. የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም፣

## 1.1. የኦዲት ሽፋን፣

### 1.1.1. የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል እና በዞን □ረጃ፣

በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በክልል/ማዕከል እና በዞን □ረጃ የተያዘው ዕቅድና አፈፃፀም በንጽጽር ከዚህ ቆዓ ሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ -1 የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣ ዞኖች እና ወረዳዎች ከ2006 ክንዉን ጋር በንፅፅር፤

| ተ.ቁ | ዞናዊ ሥርጭት | የ2006 ሂሳብ | የ2007 ሂሳብ | | ንጽጽር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክንውን | ዕቅድ | ክንውን | ከዓመቱ ዕቅድ% | የ2007 ከ2006 ክንውን% |
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | | |
| 1 | □□ልል /ማዕከል / መ/ቤቶች | **165** | **76** | **70** | **92.10** | **-57.57** |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር | **3** | **2** | **1** | **50** | **-66.67** |
| 3 | ምዕራብ ጎጃም | **21** | **18** | **16** | 88.8 | **-23.81** |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | **26** | **25** | **25** | 100 | **-3.85** |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | **37** | **21** | **20** | 95.23 | **-45.95** |
| 6 | ደቡብ ጎንደር | **20** | **16** | **16** | 100 | **-20** |
| 7 | አዊ ብሔ/አስተዳደር | **14** | **12** | **12** | 100 | **-14.29** |
| 8 | ሰሜን ወሎ | **11** | **17** | **17** | 100 | **54.54** |
| 9 | ደቡብ ወሎ | **23** | **28** | **28** | 100 | **21.73** |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | **33** | **28** | **28** | 100 | **-15.15** |
| 11 | ዋግኽምራ ብሔ/ አስተዳደር | **10** | **8** | **8** | 100 | **-20** |
| 12 | ኦሮሞ ብሔ/አስተደደር | **5** | **8** | **8** | 100 | **60** |
| | ድምር | **368** | **259** | **249** | **96.13** | **32.3** |

**ማሳሰቢ□**፣የ2007 በጀት ዓመት ክንውን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ያነሰበት ምክንያት የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ በርካታ አነስተኛ መ/ቤቶች ኦዲት በመደረጋቸው ነው።

### 1.1.2. የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር እርከን፤

**የ2007 በጀት ዓመት ዕቅድ ክንውን በአወቃቀር□እርከን□ሲ.ታ□ እንደሚከተለው ነው።**

ሠንጠረዥ 2. የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር□እርከን

| ተ.ቁ | የአወቃቀር እርከን | 2007 ሂሣብ ክንውን | |
|---|---|---|---|
| | | በመ/ቤት ብዛት | ከጠቅላላዉ ክንዉን በ% |
| **1.** | □ልል/ማዕከል | 70 | 28.11 |
| **2.** | ዞን አስተዳር | **9** | **3.62** |
| **3.** | □ረ□ | **139** | **55.82** |
| **4.** | ከተማ አስተ. | **31** | **12.45** |
| | **ትምር** | **249** | **100** |

## 1.2 የኦዲት ስልት:-

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ከጥር 1/2007 እስከ ታህሳስ 30/08 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉት 249 መ/ቤቶች ውስጥ 206 (82.73%) በንሞና እንዲሁም 43(17.27%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማና ጥያቄ ቀርቦባቸዉ በየነጥቦቹ መነሻ መሠረት በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸዉ።

የኦዲት ሥራውን ሙሉ በሙሉ በንሞና የኦዲት ስልት ለማከናወን ታቅዶ 82.73% በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረጉ ሲሆን የኦዲት ሥልቱ □ለም አቀፍ ተቀባይነትን ያገኘና በዝርዝር ኦዲት ተደርጐ ከሚገኘ□ ጥቅም ያላነሰ ውጤት ሊያስገኝ የሚያስችል ዘመናዊና በተመጣጣኝ □ስ□□ን□ልና ወጪ ሥራውን ለማከናወን ጊዜና ገንዘብ ቆ□ቢ ከመሆኑም በላይ በሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ ስጋት ያለበትን አካባቢ ትኩረት ስለሚሰጥ አዋጭ በመሆኑ ነው።

የንሞና ኦዲት ስልትን አስመልክቶ ካለፊዉ በጀት ዓመት አፈፃፀም የዕቅድ ክንውን በንጽጽር እንደሚከተለ□ ቀርቧል። ሠንጠረዥ 3. □ኦዲት ስልት፤

| ተ.ቁ. | የኦዲት ስልት | 2006 ሂሣብ | | 2007 ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ክንውን ብዛት | % | | |
| 1 | ንሞና | **334** | 90.7 | **206** | 82.73 |
| 2 | ል□ ኦዲት | 34 | 9.2 | 43 | 17.27 |
| | ትምር | **368** | **100** | **249** | **100** |

በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የ2007 ክንውን (82.73%) መሸፈኑ የሚያሣየው የኦዲት አፈፃፀሙ ዘመናዊና ወጪ ቆጣቢ አሠራር የተከተለ መሆኑን ሲሆን በዝርዝር እንዲሠሩ የቀረቡና ኦዲት የተደረጉ የልዩ ኦዲት ስራዎች ከ34 (9.2%) ወደ በ43 መ/ቤቶች /17.27%/ ከፍ ማለታቸው የልዩ ኦዲት ጥያቄዎችን የሚያቀርቡ አካላት (ዜጎችና ተቋማት) እየጨመሩና በመ/ቤታችንም ኦዲቱ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ መሆኑን ያመለክታል።

## 1.3. የኦዲት አስተያየቶች፣

የ2006 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርጎ ወጪ የሆኑ ሪፖርቶች 368 ሲሆኑ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ጋር ተነፃፅሮ እንደሚከተለው ቀጥሎ ቀርቧል፤

ሠንጠረዥ 4 የኦዲት አስተያየቶች፣

| ተ.ቁ | የኦዲት አስተያየት | የ2006 ሂሣብ | | 2007 ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | በ% | የመ/ቤት ብዛት | በ% |
| 1 | ንፁህ/አጥጋቢ | 1 | 0.27 | 5 | 2 |
| 2 | ከዚህ በስተቀር | 323 | 87.7 | 196 | 78.72 |
| 3 | አጥጋቢ አይደለም | 6 | 1.6 | - | - |
| 4 | አስተያየት መስጠት አለመቻል | 4 | 1 | 5 | 2 |
| 5 | ልዩ ኦዲት (አስተያየት የማይሰጥበት) | 34 | 9.2 | 43 | 17.28 |
| | ድምር | 368 | 100 | 249 | 100 |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተ□ረጉ 249 መ/ቤቶች ውስጥ ለ194(78.72) ከዚህ በስተቀር፣ ለ5 (2%) አስተያየት መስጠት አልተቻለም፣ ለ5 (2%) ንፁህ አስተያየት እና 43(17.28%) የልዩ ኦዲት ሥራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት የማይሰጥባቸው ናቸው።

በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2007 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር " **ንፁህ አስተያየት**" የሚለው በ1.73% መጨመሩ እና "**አስተያየት መስጠት አለመቻል**" እንዲሁም "**አጥጋቢ አይደለም**" የሚለው ካለፈው ዓመት ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው የሚያመላክት ሲሆን አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ በ8.08% መጨመሩ ህብረተሰቡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ለመታገል በክልሉ እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል። በሌላ በኩል "**ከዚህ በስተቀር**" የሚለው አስተያየት በ9.78% መቀነሱ አብዛኛው ስራ ከመደበኛ ኦዲት እየወጣ ወደ ልዩ ኦዲት ትኩረት መደረጉን ያመለክታል፡፡

**የኦዲት አስተያየቶች መገለጫዎች፤**

1. "**አጥጋቢ አስተያየት**" የሚሰጠው ይህ ነው የሚባል ግኝትና የአስራር ችግር ያልታገኘበት መ/ቤት ነው፡
2. "**ከዚህ በስተቀር**" የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው የኦዲት ሪፖርቶች ከተወሰኑ ግኝቶችና የአሠራር ችግሮች በስተቀር የተሻለ አፈፃፀም የሚታይባቸው ናቸው፡፡
3. "**አጥጋቢ አይደለም**" □ሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት /ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡
4. " **አስተያየት መስጠት አልተቻለም**" የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ደግሞ መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት እንዴት ሥራ ላይ□እንዳዋሉት የሚገልፅ የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበባቸው፣ □□ሰዓ ቁዓዓር ሥር□ታቸው በጣም የተዳከመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

   በአጠቃላይ በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተገለጹት አስተያየቶች የተሰጡባቸው መ/ቤቶች ግኝቶቻቸውና የአሰራር ችግሮቻቸው ጉልህና መሠረታዊ የሆኑባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ በሪፖርቶቹ የቀረቡት ችግሮች ጉልህና መሠረታዊ መሆናቸውን በመገንዘብ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መ□ሰት □ቷበቅባቸዋል፡፡

### 1.3.1 "አስተያየት መስጠት አልተቻለም" የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች፤

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት 249 መ/ቤቶች ውስጥ 5(2%) መ/ቤቶች የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና ስለ ሂሳቡ ትክክለኛ መሆን አለመሆን የሙያ አስተያየት ለመስጠት ባለመቻሉ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ ‹‹**አስተያየት መስጠት አልተቻለም**›› የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር እና ለአስተያዩቱ ዋና ዋና ምክንያቶች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 1.3.1.1 ቋሪት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ  ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለሁለት ሂሳቦች የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያለመዘጋጀቱ፣
- ለኦደት ስራ ያልቀረቡ 33.36 ጥራዝ ደረሰኞች ብር 161,597.20፣
- ለኦዲት ስራ ተፈልገው ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች ብር 321,035.81፣

- የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ተከፋይ ሂሳብ ብር 558,000.00፣
- ለእንስሳት ጤና አገልግሎት፣ለስፖርት ምክር ቤት እና ለተባበሩት መንግስታት ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅላቸው መሆኑ፣
- የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያለመቻሉ፣መገኘቱ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

**1.3.1.2 አዴት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 636,550.39፣
- አላግባብ የተከፈለ ልዩ ልዩ ወጭዎች ብር 511,752.77፣
- ያለምንም ማስረጃ ተከፈለ ወጭ ብር 98,865.00፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 672,131.13፣
- የተሰብሳቢ እና የተጣራ ሃብት ሂሳብ ሪፖርት በሌጀርና በሪፖርት መካከል የታየ ልዩነት ብር 10,371.19 እና 176,494.03፣
- የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድር አለመቻሉ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

**1.3.1.3. አዴት ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት**

- ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የገቢ ደረሰኝ ብር 9,212,289.14፣መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

## 1.3.1.4 ደንበጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ያለምን ማስረጃ በወጭና በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ የተገኘብር 259,155.34፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተስብሳቢ ሂሳብ ብር 515,215.85፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተከፋይ ሂሳብ ብር 353,151.98፣
- የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

## 1.3.1.5. ምስራቅ በላሳ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ  ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የመደበኛ ሂሳብ ጂ.ኦ.ቪ 1000078581992፣ የትምህርት ጥራት ጂ.ኦ.ቪ 10000785882034፣መሰረታዊ አገልግሎት ማሻሻያ ሂሳብ ጂ.ኦ.ቪ 1000103378005፣ የተዘዋዋሪ ብድር ማስፈፀሚያ ሂሳብ ጂ.ኦ.ቪ 1,000078582018፣የተባበሩት መንግስታት ሂሳብ ጂ.ኦ.ቪ 1000078582058 እና የእንስሳት ጤና አገልግሎት ማስፈጸሚያ ሂሳብ ጂ.ኦ.ቪ 1000078580079 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣
- ለኦዲት ሥራ ያልቀረቡ 16 ጥራየስፖርት ምክር ቤት ገቢን ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ተቀጽላ  ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ 15,310,305.13፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ የተገኘ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,093,679.64፣
- በብልጫ የፀደቀና የተከፈለ ወጪ ብር 3,237.07፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበልና የስልጠና አበል ብር 116,010.00፣
- ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 996,829.92፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የወጭ ሰነዶች ብር 9,474,009.60፣

- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ 1,951,829.81፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ የተገኘ የተከፋይ ሂሳብ ብር 373,570.12፣
- ለሰተባበሩት መንግስታት ሂሳብ ፣ለእንስሳት ጤና አገልግሎት፣ለሰተዘዋዋሪ ብርድ ማስፈጸሚያ ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅላቸው መሆኑ፣መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

## 1.4. መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች፣

ይህ ሪፖርት ወጪ እስከተደረገበት ሰኔ 30/2008 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የክልል /ማዕከል/ መ/ቤቶች**

1. ትምህርት ቢሮ ( MDG 2007)
2. ጤና ጥበቃ ቢሮ ( MDG 2007)
3. መንዝ ላሎ ምድር ወረዳ ፍድ ቤት (2006)

**ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳር**

4. **እነብሳ ሳር ምድር ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
5. **ስሀናን ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
6. **ብቸና ከተማ** አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር**

7. **ጎንደር ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት (2006)**
8. **ጣቁሳ ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
9. **ምዕራብ በለሳ ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳዳር**

10. ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር**

11. ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
12. ዳውንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
13. ላሊበላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር**

14. አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
15. ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
16. ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
17. አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
18. አሳግርት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር**

19. አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር**

20. ሰቆጣ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት (2006)
21. ጋዝጊብላ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት (2006)
22. ዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
23. ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

በአጠቃላይ መልስ አሰጣጡ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉ 334 መ/ቤቶች 99(29.64%) መልስ ካልሰጡ መ/ቤቶች ጋር ሲነጻጸር በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 206 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 23(11.16%) ስለሆኑ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል የታየበት ቢመስልም ለዚህ ዋና ምክንያት ግን የክልሉ ገንዘብና ኢ/ል/ት/ቢሮ ባደረገው ከፍተኛ ርብርብ ሲሆን ለወደፊቱ የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት በማያከብሩ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት ላይ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ሌላው በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 43 መ/ቤቶች ሲሆኑ በፍትህ አካላት በኩል እና እንደሁኔታው በኦዲት ተደራጊ ተቋማት በኩል የተወሰደውን እርምጃ የማሳወቁ ልምድ ለወደፊቱ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡

## 1.5 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

### 1.5.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ብል□ ፣

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን በየጊዜው ቁጥጥር እያደረጉ መያዝ ይጠበቅባቸዋል። በዋና ኦዲተር መ/ቤት በኩል የበጀት ዓመቱን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማረጋገጥ ተግባር ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ያለ ተግባር ነው። በተጨማሪም በአንዳንድ የኦዲት ሥራዎች ላይ ሁኔታዎች ትኩረት ሲሰጡና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲረጋገጥ በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በወቅቱ በመቀበል የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማመዛዘን ተግባር የሚከናወን ሲሆን የኦዲት ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 5 □ሬ ገንዘብ ቶድለትና ብል□ ፣

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው ማዕከል ዞን | ጉድለት | | | | ከገንዘብ □ዬ ብል□ | የሌጀር ከወጪ ቀሪ ከቆጠራ ልዩነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | □መ/ቤ ትብዛት | ከአሁን ገንዘብ □ዬ | ከቀድሞ ገንዘብ ያዥ | ድምር | | በመብለጥ | በማነስ |
| 1 | ክልል ማዕከል | 3 | 1,760,862.72 | 1,252.89 | 1,762,115.61 | | 12,336.27 | |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ | | | | | | | |
| 3 | ምክ/ጐጃም | | | | | | | |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | 1 | 486,803.33 | | 486,803.33 | | 77,303.08 | 500.00 |
| 5 | ሰሜን ጉንደር | 1 | 173,027.00 | | 173,027.00 | - | 938,085.48 | |
| 6 | ደቡብ ጎንደር | | | | | | | |
| 7 | የአዊ ብሔ/አስተ/ | | | | | | 586,209.04 | 6,000.00 |
| 8 | ሰሜን ወሎ | 1 | | 977.71 | 977.71 | | 2,229,176.74 | 2259.50 |
| 9 | □ቡብ ወሎ | 5 | 636,349.63 | 40,235.17 | 676,584.80 | | 5,603,746.51 | 1,111,816.93 |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | | | | | | | |
| 11 | ኦሮሞ ብሔ/አስተ/ | | | | | | | |
| 12 | ዋግኽምራ ብሔ/አ | | | 79,528.46 | 79,528.46 | | | |
| ድምር | | **11** | **3,057,042.68** | **121,994.23** | **3,179,036.91** | | **9,434,520.85** | **1,120,576.43** |

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,179,036.91 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀትሞ ገንዘብ ያዦች ብር 121,994.23 በጉድለት ተገኝቷል። እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ17 መ/ቤት ብር **9,434,520.85** **የሌጀር ከወጪ ቀሪ** በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ4 መ/ቤት በማነስ ብር 1,120,576.43 ተስተውሏል። (ዝርዝሩን (አባሪ 2 ይመልከቱ።)

**የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየባቸው መ/ቤቶች** የከሚሴ መምህራን ትምህርት ኮላጅ ብር 1,693,403.72 የኮሌጁ ዋና ገንዘብ ያዥ ስራ ከጀመሩበት ከ18/01/02 እስከ 24/06/2007 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ደብረ ማርቆስ ከተማ ውሃ ፍሳሽ አግልግሎት ጽ/ቤት ብር 479,759.20 ከ27/06/2001 እስከ 16/11/2006 ዓ.ም የቢል ሽያጭ ባለሙያ ሁነው ሲሰሩ ቢል ሽጠው የሰበሰቡትን ገቢ ለገንዘብ ያዥ ገቢ በሚያደርጉበት ወቅት ኦርጅናል /በራሪ/ የገቢ ደረሰኝ ቅጠሉ ላይ ከፊት ለፊት ቁጥር በመጨመር እና ፊደል በመደለዝ እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ ለገንዘብ ያዥ ሳያስረክቡ ለግላቸው በመጠቀም የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ አንዳሳ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር 35,500.00 አንድ ግለሰብ ብዛት 2,839

ብር 14,195.00 የደሮ ጫጩት ከማዕከሉ ግዥ ፈጽመው እና ከዚህም በተጨማሪ ለደሮ ማንንዣ በሚል ከማዕከሉ ዋና ገንዘብ ያዥ በጥሬ ገንዘብ ያለአግባብ ብድር ብር 21,305.00 በመውሰድ በድምሩ ብር 35,500.00 በዓባይ ባንክ፣በከፈቱት የባንክ ሂሳብ ቼክ ቁጥር AF3149946 ገንዘብ ሳይኖራቸው እንዳላቸው በማስመሰል ደረቅ ቸክ በመስጠት የተጭበረበረ እና የጎደለ ጥሬ ገንዘብ ፣አዲአርቃይ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 27,290.73 የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ ሁነው ከ04/06/2003 እስከ 06/4/2007 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ደልጊ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ብር 173,027.00 ከ27/7/2003 እስከ 17/2/2006 ዓ.ም ድረስ ዋና ገንዘብ ያዥ ሁነው ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 40,235.17 ዋና ገንዘብ ያዥ ስራ ከጀመረበት ከ17/08/2005 እስከ 5/07/2006 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ሲርባ መነብኮ አጠ/1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 17,876.64 ከ1996 እስከ 17/10/2002 ዓ.ም የትምህር ቤቱ ገንዘብ ያዥ ሁነው ሲሰሩ ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ወረባቦ ወረዳ ገጠር መንገድ ልማት ጽ/ቤት ብር 34,416.30 ከ08 ቀበሌ ተነስቶ 010 እስከ 011 ቀበሌ የመንገድ ግንባታ ሲከናወን የወረዳው ገጠር መንገድ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የነበሩት ለመንገድ ስራ ገንዘብ ከተለያዩ ቀበሌ አስተዳዳሪዎች የሰበሰቡት እና ወጭ ያደረጉት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣አልቡኮ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ብር 366,825.96 ስራ ከጀመሩበት ከ24/4/2005 እስከ ለቀጣይ ገንዘብ ያዥ እስከአስረከቡበት 21/9/2006 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ምስራቅ በለሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 4,668.27 ከ01/10/2000 እስከ 28/06/2006 ዓ.ም ዋና ገንዘብ ያዥ ሁነው ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ የሳህላ ሰየምት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ብር 79,528.46 የቀድሞው ረዳት ግንዘብ ያዥ የነበሩት ከ2/11/2002 እስከ 11/11/2003 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣ የቦረና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ብር 10,643.28.00 የኮምባይን ዴስክ አሰሪ ኮሚቴ በመሆን ያለህጋዊ ውክል በነጭ ወረቀት ከየትምህርት ቤቱ ለኮምባይን ዴስክ ማሰሪያ የተሰበሰበውን ገቢ ለግል ጥቅም በማዋል የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ የኮምቦልቻ ቁ.2 አጠ/1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 10,957.45 የት/ቤቱ የቀድሞ ገ/ያዥና እቃ ግዥ ሰራተኛ ስራ ከጀመሩበት ከ14/06/04 እስከ 24/11/05 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣የቃሉ ወረዳ ንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ብር 195,630.00 የንግድ ማህበራት ምክር ቤት በባለሙያነት በሚያደራጁበት ወቅት የገቢ ደረሰኝ በማሳተም ገቢን ከአባላቱ በመሰብሰብ ለግል ተጠቅመው በመገኘታቸው የጥሬ ገንዘብ ሂሳቡ ሲመዛዘን በጉድለት የተገኘ ሲሆን ከጥሬ ገንዘብ ጉድለት ጋር በተያያዘ ለግኝቶች በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱት፤

- ለዕለት ሥራ እንቅስቃሴ ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ጥሬ ገንዘብ በካዝና ማስቀመጥ፣
- ገንዘብ ያዦች የራሳቸዉ መከታተያ የካዝና መቆጣጠሪያ መዝገብ እንዲይዙ አለማድረግ፣
- በየጊዜው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማድረግ ከተያዘው የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር አለማድረግ፣

- በዕለት ገቢ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበው ገንዘብ ለባንክ ወይም ለዋና ገንዘብ ያዥ በወቅቱ ገቢ/ፈሰስ አለማድረግና ለረጅም ጊዜ በእጅ በማቆየት ለግል መጠቀሚያ መዋሉና በመጨረሻም ጉደለት መገኘቱ፤
- በተለይ ለረዳት ገንዘብ ያዥና ለግዥ ሠራተኞች በቼክ የመክፈል ልምድን አለመዳበርና ከዋና ገ/ያዥ ጥሬ ገንዘብ በቅድሚያ ከፍያ ሰነድ በሚሰጥበት ወቅት ሂሳቡ ተወራርዷል አልተወራረደም በሚል የመካከድ ሁኔታ መፈጠር፤
- የገንዘብ ያዥ ለውጥ ሲደረግ በተገቢው ርክክብና የሂሳብ ምርመራ አለማስደገፍ፤እንዲሁም በገቢደረሰኝ
- በወጪ ቫውቸሮችና ሌጀሮች የተሰራበት መጨረሻ ገጽ ላይ የመለያም ልክትና ፊርማ (cut-off ) አለማድረግና አለመፈራረም፣
- የባንክ ሂሳብ ሌጀር አለመያዝና በየወሩ ባንክ ከሚልከው ሂሳብ መግለጫ ጋር አለማስታረቅ፣
- ከትምህርት ቤቶች እና ከታዳጊ ጤናጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች የሚሰበሰብ ገንዘብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር አለማድረግና መድሃኒትና ገንዘብ በአንድ ባለሙያ መያዝ ብሎም የተሰበሰበ ገቢ ለረዥም ጊዜ በእጅ ላይ በማቆየት ለብክነት መዳረግ፤
- በባንክ ገቢ ደረሰኝ /ስሊፕ/ ላይ ቁጥር በመጨመር ባንክ ከገባው ገንዘብ አስበልጦ የገቢ ደረሰኝ ማስቆረጥ እና ልዩነቱን ለግል ጥቅም ማዋል፣
- ቀድሞ የተከፈሉና የተወራረዱ የሂሳብ ማስረጃዎችን /የፔይሮል/ ገጾችን ገንጥሎ እንደገና በወጪ በማጸደቅና በዚያው ልክ ገንዘብ ለግል በመውሰድ፤
- በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የእለት እለት እንቅስቃሴ ላይ በፋይናንስ ኦፊሰሮችም ሆነ በውስጥ ኦዲተር የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ማነስ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ከገንዘብ ያዦች የሚፈለገውን ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሠረት ብር 21,305.00 የተመለሰ ብር 136,859.00 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ያለ መሆኑና በተለይ በደብረ ማርቆስ ከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት በአጥፊዎች ላይ የእስራትና የገንዘብ ቅጣት የተወሰነባቸው ሲሆን በሌሎች ጉዳዩች ላይ ግን ይህ ሪፖርት እስከተጠናከረበት 30/10/08 ዓ.ም ድረስ ግልጽ ምላሽ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣**

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ሂሳባቸውን በኦዲት ለማመዛዘን ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፣

## የክልል ማዕከል መ/ቤቶች

1. ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ
2. አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
3. መርጦ ለማርያም ግብርና ኮሌጅ
4. ሳንጃ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ
5. ቆላድባ ቴ/ሙያ ኮሌጅ
6. ቻግኒ ዳልጋ ከብት
7. አንዳሳ ደሮ ብዜት ማዕከል
8. ጐንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
9. ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል
10. ቦሩ ሜዳ ሆስፒታል
11. አቃስታ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠና ኮሌጅ
12. ቆቦ ግብርና ምርምር ንዑስ ማዕከል
13. ወይዘሮ ስህን ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ
14. ሲርንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል
15. አጅባር ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠና ኮሌጅ
16. መካነ ሰላም ሆስፒታል
17. ሰቆጣ ዝናብ አጠር ግብርና ምርምርማዕከል
18. መንዝ ላ ወረዳ ፍርድ ቤት
19. ራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት

**ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር**

20. ሜጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
21. ጃቢ ጣህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
22. ቋሪት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
23. ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
24. ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
25. ቡሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
26. ደጋ ዳሞት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
27. ደንበጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር**

28. ቢቡኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
29. ባሶ ሊበን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
30. ደባይ ጥላት ግን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
31. አነደድ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
32. ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
33. ሰሜን ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
34. ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
35. ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
36. አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
37. ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
38. ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
39. ጃናሞራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር**

40. አንዳቤት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
41. ደቡብ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
42. ታች ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
43. ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
44. ምስራቅ እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
45. ወረታ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**አዊ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር**

46. **አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
47. ጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
48. ዳንግላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር**

49. ደቡብ ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
50. ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
51. ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
52. ለገሂዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
53. ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
54. ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
55. ለጋንቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
56. ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
57. ደሴ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
58. አልቡኮ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር**

59. **ላስታ ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
60. ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
61. ግዳን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
62. ሰሜን ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
63. መርሳ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
64. ሐብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
65. ወልድያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
66. ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር**

67. አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር**

68. ዳዌ ሀረዋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
69. ደዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
70. ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
71. ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር**

72. ሳህላ ሰየምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
73. ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ከላይ በተዘረዘሩት 73 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2007 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ሲሆን ለዚህም ዝርዝር ምክንያቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

- የተሟላ የሂሳብ መዝገብ /ሌጀር/ ተዘጋጅቶ የሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገና ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ ሊያመለክት ባለመቻሉ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና እንደጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላና ህጋዊ ቆጠራ ባለመደረጉ፡
- ገንዘቡ በአንድ ገንዘብ ያዥ ተይዞ እየተዳደረ ባለበት ሁኔታ የውስጥ ገቢን ሳይጨምር የመደበኛ ጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ብቻ ነጥሎ ቆጠራ የሚደረግ በመሆኑ፤
- በገንዘብ ያዥ የሥራ መደብ ላይ በርካታ ሠራተኞች እየተለዋወጡ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን ያንቀሳቀሱ ሲሆን ርክክብ በተፈፀመበት ወቅት በገቢ ደረሰኞች፤ በወጪ ቫውቸሮችና በጥሬ ገንዘብ መከታተያ ሌጀሮች ላይ ርክክብ በተደረገበት ዕለት በጋራ በመፈራረም የመለያ /Cut-off/ ምልክት ያልተደረገ መሆኑእና ገንዘብ ያዦች በሚቀያየሩበት ወቅት ርክክብ ሲፈፀም የጥሬ ገንዘብ ሌጀር የሚያሳየው ከወጪ ቀሪ በቆጠራ እየተረጋገጠ ርክክብ የማይፈፀም መሆኑ፣

- ኦዲት አስደራጊዎች በኦዲት ወቅት የገቢና የወጪ ሂሣቡን መዝግበው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ምዝገባውን አጠናቀው ለማቅረብ አለመቻላቸው፣
- የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሣቦች ከወጪ ቀሪያቸውን የሚያሣይ መቆጣጠሪያ የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው ሆኖ መገኘቱ፣
- ለረጅም ዓመታት እየተንከባለለ የመጣ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ ሌጀርና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ልዩነት የፈጠረ ቢሆንም በውስጥ ኦዲተሮች አማካይነት መንስኤው ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻሉባቸው ስለሆኑ መ/ቤቶቹ አሰራራቸውን እንዲያስተካክሉና በየጊዜውም በውስጥ ኦዲተሮቻቸው እየተከታተሉ የጥሬ ገንዘብ አስተደደራቸውን እንዲያሻሽሉ በየሪፖርቱ አሳስበናል፡፡

**1.6.2. ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ቢ፤**

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 249 መ/ቤቶች □ስዓ በ69 መ/ቤቶች ብር 59,328,259.60 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ □ር□ሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 6 በውዝፍ የሚገኝ ቢ፣**

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | የ2006 በውዝፍ የሚገኝ/ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ | | | የ2007 በውዝፍ የሚገኝ/ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 1 | 3,471.22 | 0 | 5 | 209,079.70 | 0.35 |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ | - | | 0 | | - | |
| 3 | ምክ/□ጃም | 6 | 290,704.42 | 0.00 | 6 | 105,786.04 | 0.17 |
| 4 | ምሥ/□ጃም | 8 | 8,143,077.78 | 0.07 | 6 | 89750.03 | 0.15 |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 8 | 37,953,632.53 | 0.34 | 6 | 50,487,477.56 | 85.10 |
| 6 | ደ/ጎንደር | 7 | 1,846,589.29 | 0.01 | 4 | 27,657.07 | 0.05 |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 1 | 230,071.63 | 0.00 | 6 | 391,469.08 | 0.66 |
| 8 | □ቡብ □ሎ | 4 | 441,093.08 | 0.00 | 6 | 79,867.61 | 0.14 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 3 | 178,528.37 | 0.00 | 15 | 1,156,930.08 | 1.95 |
| 1ወ | አዊ ብሔረሰብ | 1 | 1,710,550.49 | 0.01 | 4 | 3,026,647.54 | 5.10 |
| 11 | ዋግ ኽምራ | 2 | 62,723.09 | 0.00 | 5 | 405,083.09 | 0.68 |
| 12 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 2 | 59,703,523.75 | 0.53 | 5 | 3,348,511.80 | 5.65 |
| ትምር | | 43 | **110,563,965.65** | **100** | **68** | 59,328,259.60 | **100** |

ከላይ ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለ□ የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 249 መ/ቤቶች □ስዓ በ68 መ/ቤቶች ብር 59,328,259.60 ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 50,487,477.56፣ኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ብር 3,348,511.80፤ አዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ብር 3,026,647.54 እና ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ብር 1156,930.08 ከፍተኛውን ትርሻ ይይዛሉ፡፡

መንግሥት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን ከተሰጣቸው መ/ቤቶች ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደውን በታሳቢነት በመያዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በገቢ አሰባሰብ ላ□ መንግሥት ያደረጋቸውን የገቢ ግብር ማሻሻያዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት ተገልጿል፡፡ ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ ብር 49,264.05(0.08%) ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 59,278,995.55 የተሰበሰበ ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተጠናከረበት ሰኔ 30/2008 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልተሰጠበት ነው፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ፡፡)

### 1.6.3 ያለማስረጃ የተሰበሰበ ገቢ፤

ማንኛውም ገቢ ከመሰብሰቡ አስቀድሞ ስለገቢው ህጋዊነት እና ስለመጠኑ ትክክለኛነት (ታሪፍ) የሚያስረዳ እንደ መድሃኒት ማዘዣ፤የገቢ አሰባሰብ ውሳኔ ወዘተ ምን ያህል ሊሰበሰብ እንደሚገባ የሚገልጽ ማስረጃ ሊኖር ሲገባ ይህ በሌለበት ሁኔታ ከ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 21,053.07 የገቢ ሂሳብ ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡

ያለማስረጃ ገቢ ከተሰበሰበባቸው መ/ቤቶች መካከል ግዳን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,595.17 እና ላሊበላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 13,394.90 ምንጩ ያልታወቀና በሚጠበቀው መጠን ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ገቢ ከፍ ያለ ድርሻ በመያዝ የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

በመሆኑም ለገቢው አግባብነት ያለውና መሰብሰብ ያለበትን መጠን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያያዝለት ለመ/ቤቶች በኦዲት ሪፖርቱ አሳስበናል፡፡ሆኖም ስለማስረጃው መያያዝ በምላሾች አልተገለጸም፡፡

### 1.6.4. ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ እና የሥራ ገቢ ግብር፤

በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር እንዲሁም ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሲከፈል መሰብሰብ የነበረበት የስራ ግብር ከ51 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 923,723.55 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ካሳሰብን በኋላ ብር 48,329.82(5.23%)ብቻ እንደተሰበሰበ ከግብረ መልሱ መረዳት የተቻለ ሲሆን ቀሪው ብር 875,393.73 በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

### 1.6.5 ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፣

ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ73 (35.43%) መ/ቤቶች ብር 27,435,531.20 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ጎንደር ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 10,77,7031.65 የያዙ 582.76 ጥራዝ የገቢ ግብር የተሰበሰበባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ፣አዴት ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 9,212,289.14 የያዙ የገቢ ግብር የተሰበሰበባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ደብር ማርቆስ ከተማ

አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,494,904.55 92 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት ገቢ የተሰበሰበባቸው እና 2340 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ፣ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 673,843.05 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ራያ ቆቦ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 660,040.00 የገቢ ግብር የተሰበሰበባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ሐብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 212,807.55፣ወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 241,680.90 የያዙ 11.49 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ የተሰበሰበባቸው እና 264.04 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ ደረሰኞች፣ታች አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፈ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 656,138.34 የያዙ የያዙ 3 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ፣ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 257,021.00 የያዙ 53.78 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ የተሰበሰበባቸው እና 165.88 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የገቢ ደረሰኝ መደበኛ እና የስፖርት ምክር ቤት ብር 24,182,753.18፣ ከ200,000.00 ብር በላይ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ይህም ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ደረሰኞቹ ቀርበው የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም ደረሰኙ ስለመቅረቡም ሆነ ስለመረጋገጡ በአጠቃላይም ስለተወሰደው እርምጃ በምላሹ አልተመለከተም፡፡

## 1.7. የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት፤

### 1.7.1. በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ94 መ/ቤቶች ብር 828,281,282.42 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡ (ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል)፤

**ሠንጠረዥ 7 በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ሂሣብ፤**

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2006 ሂሣብ | | | 2007 ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 24 | 8,800,652,605.6 | 94.58 | 18 | 234,485,060.48 | 28.31 |
| 2 | ባሕር ዳር ከተማ | 2 | 1,965,192.94 | 0.02 | | - | 0 |
| 3 | ምክ/□ጾም | 9 | 92,506,136.85 | 0.99 | 4 | 3,382,928.46 | 0.41 |
| 4 | ምሥ/□ጾም | 6 | 28,574,323.78 | 0.31 | 12 | 91,103,258.64 | 11.00 |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 12 | 82,836,193.39 | 0.89 | 7 | 83,978,494.27 | 10.13 |
| 6 | ደ/ጎንደር | 5 | 43,219,914.48 | 0.46 | 8 | 97,363,153.95 | 12.00 |
| 7 | አዊ ብሔረሰብ | 4 | 20,146,752.41 | 0.22 | 6 | 39,735,281.26 | 4.80 |
| 8 | ሰሜን ወሎ | 2 | 21,380,722.55 | 0.23 | 9 | 69,313,090.62 | 8.37 |
| 9 | □ቡብ □ሎ | 10 | 94,853,533.82 | 1.02 | 11 | 96,543,582.24 | 11.91 |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | 17 | 115,586,999.10 | 1.24 | 11 | 60,296,687.38 | 6.07 |
| 11 | ኦሮሞ ብሄረሰብ | | | 0 | 3 | 22,601,971.37 | 3.00 |
| 12 | ዋግኸምራ ብሔረሰብ | 1 | 3,400,842.63 | 0.04 | 5 | 29,477,773.75 | 4.00 |
| ድምር | | 92 | 9,305,123,218.00 | 100 | 94 | 828,281,282.40 | 100 |

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተመለከተው በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ከፍተኛ ተሰብሣቢ ሂሣብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል አብክመ ፖሊሰ ኮሚሽን ብር 100,193,818.09፣አብክመ ፖሊስ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ብር 10,808,272.72፣ አብክመ ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ /MDG/ ቢሮ ብር 108,727,453.18፣ ጎንቻ ሲሶ እነብሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 20,939,334.24፣ ደባይ ትላት ግን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 15,262,476.70፣ እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 18,056,669.20፣ ላይ አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,692,034.05፣ አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 13,204,489.66፣ ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 11,734,669.16፣ ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 30,408,349.96፣ ጃናሞራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 16,512,725.01፣ ደቡብ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 14,219,189.45፣ ሊቦከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 23,339,025.40፣ ምስራቅ እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 17,197,988.72፣ ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 18,258,749.58፣ ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 14,431,020.04፣ ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12,111,413.29፣ ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12,686,625.39፣ ወግዲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 23,690,581.80፣ ግዳን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12483125.84፣ ሰሜን ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,946,411.75፣ ወልድያ ከተማ አሰ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 21,583,609.57፣ ግሽራቤል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብ 10,226,089.05፣ ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 11,487,783.89፣ ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12,006,086.42፣ አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12,617,228.67፣ ሰቆጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10216,836.95 ከ10 ሚሊዩን ብር በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ ወይም የመወገጃ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በቁጥር 6/2004 በክፍል 4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ገልጸናል፡፡ ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ23 መ/ቤቶች ብር 51,904,941.96 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡ ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሣቦች መካከል ደብረማርቆስ ከተማ አስነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ ብር 10,103,271.91፣ ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 21,686,821.39፣ ዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 5,897,921.35 ከ5 ሚሊዮን ብር  በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡

ይህም ሂሳቡ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በመገምገም በሚገኘው ውጤት መሠረት እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ያስገነዘብን ቢሆንም የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ የተሰጠ ምላሻ የለም፡፡

### 1.7.2 ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ 4ቱ ብር 12,320,690.78 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣(መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ) ሳይቀርብለት በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ይኸው ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች መካከል ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሠ/ማዕከል ብር 8,188,022.32፣ ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሠ/ማዕከል ብር 3,948,909.96፣ ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ በመያዝ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከተጠቀሰዉ ሂሳብ ዉስጥ የነጠላ ፋይናንስ አደረጃጀት በተጀመረበት ወቅት ከየሴክተሮቹ ሂሣብ ክፍል በርክክብ የመጣ፣የግብዓትና የተዘዋዋሪ ብድር ሂሣብ መሆኑንና በወቅቱ ሂሳቡ ከማን እንደሚሰበሰብ መቼ እና ለምን የተሰጠ እንደሆነ የሚያሳይ ሰነድ/ማስረጃ እንዳልተያያዘለት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም ለሂሳቡ ትክክለኛ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ካለ እንዲያያዝና በየባለዕዳዎቹ ስም ተይዞና ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ ወይም እንዲወገድ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚገልጽ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

### 1.7.3 በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ67 መ/ቤቶች ብር 537,949,080.04 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መለልስ እንደተረጋገጠው ብር 11,878,485.59 ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲሆን ቀሪው ብር 526,070,594.45 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ድረስ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

**ሠንጠረዥ 8 በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

| ተ.ቁ. | በክልል ማዕከላትና ዞን | የመ/ቤቱ ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 9 | 199,212,121.55 | 37.03 |
| 2 | ምዕራብ ጎጃም | 7 | 56,317,916.94 | 10.47 |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | 11 | 31,908,038.83 | 5.93 |
| 4 | ሰሜን ጎንደር | 11 | 107,766,497.94 | 20.04 |
| 5 | ሰሜን ወሎ | 1 | 2,366,840.54 | 0.44 |
| 6 | ሰሜን ሸዋ | 9 | 27,891,026.16 | 5.18 |
| 7 | ደቡብ ጐንደር | 9 | 82,748,677.74 | 15.38 |
| 8 | ደቡብ ወሎ | 4 | 4,326,792.64 | 0.80 |
| 9 | ኦሮምያ ብሔረሰብ ዞን | 3 | 9,251,364.81 | 1.72 |
| 10 | አዊ ብሔረሰብ ዞን | 1 | 12,628,161.13 | 2.35 |
| 11 | ዋግኽምራ | 2 | 3,531,641.76 | 0.66 |
| 12 | ባ/ዳር | - | - | |
| | **ድምር** | **67** | **537,949,080.04** | **100** |

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ ጃቢ ጣህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,498,187.38፣ ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር

10,877,253.45፣ ቡሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 18,961,443.25፣ አዋበል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 10,065,878.92፣ አነደድ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 11,352,106.08፣ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15310305.13፣ ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 22,760,863.09፣ ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 12,925,420.83፣ወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 24,341,764.83፣ ሊቦከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 19,854,471.60፣ፋርጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 12,847,853.51፣ላይ ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 21,886,603.51፣ምስራቅ እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 11,039,703.16፣ ዚገም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,262,8161.13፣ኤፍራታ ግድምወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 12,538,226.60 ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ ገላጭ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ ወይም ለማስወገድ የማያስችል በመሆኑ የተሻሻለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል ላለፈውም ሆነ ለወደፊቱ ክትትል እየተደረገ መሰብሰብ/መወገድ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ (አባሪ2 ይመልከቱ)

## 1.8. ወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፣

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የወጪ ሂሳብ የአሠራር ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.8.1 የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት *የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ11 መ/ቤቶች ብር 20,738,029.49 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **በሰሜን ጐንደር ዞን ላይ አርማጭሆ ወረዳ የትክል ድንጋይ መሪ መዘጋጃ ቤት** ብር 2,500,000.00 ከሹማሪ-ገንብራ አዲስ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ለስራ ተቋራጭ ማህበር ቅድሚያ ክፍያ ሲከፈል የጨረታ ስርዓት ሳይሟላና በባዶ ቅጽ ላይ ውል በመያዝ አላግባብ የተከፈለ እና ስራው ሳይጀመርና ሳይሰራ በመቅረቱ ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ መገኘቱ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም የፍትህ አካላት በዚህ ጉዳይ ላይ ገና ምላሽ ስላልሰጡ (ሪፖርቱ በቅርብ የደረሳቸው በመሆኑ) ጉዳዩ ያለበትን ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡
- **አነደድ ወረዳ ውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት** ብር 99,900.00 የውሃ ፓምፖች ግዥ ሲፈፀም የአሸናፊው አቅራቢ ድርጅት የንግድ ስራ ፈቃድ እና የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ማስረጃ ሳያቀርብ አሸናፊ ሆነው የተመረጡ፣ ንብረቱ በስፔሲፊኬሽን መሰረት መገዛቱ ሳይረጋገጥ የጥራት ችግር እያለበት ገቢ የተደረገና ጥቅም ላይ ሳይውል የተገኘ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጦ ወደ ሚመለከታቸው አካላት የተላከ ሲሆን በፍትህ ቢሮ በኩል ተጨማሪ ማስረጃ በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ በሰጡት ምላሽ ላይ ገ ልጸዋል ፡፡
- **የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ** ብር 179,372.50 የወቅቱ የገበያ ዋጋ ሳይጠና እና በወጣው የጨረታ ግዥ ሂደት አንድ ተጫራች በተሳተፋበት እና አሸናፊ በሆኑበት ሂደት በተጋነነ ዋጋ የተፈፀመ የፎቶ ኮፒ፣ፕሮጀክተር፣ፕሪንተር፣ላፕቶፕ እና ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተር ግዥ መገኘቱ በኦዲት

ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም ፡፡

- ***የእንጅባራ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ*** ብር 7,716.65 ሰራተኞች የአመት ረፍት ላይ ሁነው የትርፍ ስዓት ስራውን ለመስራታቸው የስዓት መከታተያ ሰነድ ከየስራ ክፍሉ ሳይቀርብ እና ሶስተኛ ወገን ስለክፍያው ትክክለኛነት ግልጽ ማስረጃ ማግኘት በማይችልበት ሁኔታ የመንግስት ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲውል በመታዘዙ እና ብር 10,036.61 ስልጣንን ያላግባብ በመጠቀም ባልተፈቀደ የስራ መደብ ላይ አንድ ሰራተኛ መድቦ በማሰራት የትርፍ ስዓት እና የማትጊ ክፍያ እንዲከፈል በመደረጉ ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም ፡፡
- ***የአብክመ ገጠር መንገድ ባለስልጣን*** ብር 702,843.33 የተለዩ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች ተከናውነው ለተቋራጮች በውሉ መሰረት ክፍያ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈፀመ፤ ብር 386,277.41 የኮንስትራክሽን ደርጅቱ በብድር ወስዶት ከነበረው ስሚንቶ እና ብረት ሂሳብ ውስጥ ሳይመለስ የቀረ ሂሳብ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት የተላከ ሲሆን በፍትህ ቢሮ በኩል ተጨማሪ ማስረጃ በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል ፡፡
- ***ዳባት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ*** ብር 5,000.00 የኮሌጁ ሻይ ቤት ግንባታ ሲከናወን ግንባታውን ለማከናወን ከተመረጠው አናፂ ጋር ውል ተይዞ እያለ የንግድ ስራ ፍቃድ የሌለው ሆኖ በመገኘቱ በቅጣት ከፍተኛ ገንዘብ ይከፍላል ብሎ በማሰብ ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው አናፂ በማስመጣት እንደገና አዲስ ውል በመያዝ ስራውን ሳያከናውን እንዳከናወነ በማስመሰል የሃሰት ሰነዶችን በማዘጋጀት የተፈፀመ ክፍያ መገኘቱ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም ፡፡
- ***ደራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስማፅከል*** ብር 469,998.42 ቀደም ሲል ስራው እንደተጠናቀቀ እና ሙሉ ክፍያው እንደተፈፀመ ለሚታወቅ የቢሮና አዳራሽ ግንባታ በውሉ መሰረት ለተቋራጩ ክፍያ ተፈጽሞ እያለ የቢሮው ግንባታ ስላላቀ በሚል ከመጀመሪያ የጨረታ ሰነድ የነበረውን የአማርኛ የስራ ዝርዝር ዋጋ ወደ እንግሊዘኛ በመቀየር በድጋሜ በውስን ጨረታ በማውጣት እና ከአሸናፊ ድርጅት ጋር ያለ ፍትህ ጽ/ቤት እውቅና ውል በመያዝ ለአንድ ግንባታ በድጋሜ የተፈፀመ ክፍያ መገኘቱ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም ፡፡
- ***የወረባቦ ወረዳ ገጠር መንገድ ልማት ጽ/ቤት*** ብር 158,137.08 የመንገድ ጠረጋ ስራ እነ ለዲች ቦይ ግንባታ ለማከናወን ጨረታውን ለአሸነፈው ተቋራጭ ከተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ያልተመለ ገንዘብ፤ ብር 35,213.53 ከመንገድ ጋር ተያያዝ ለሆኑ ለዲች ቦይ፣ካልቨርትና ካናል ስራዎች ለካናወነው ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተከፈለ፣ብር 68,800.00 ከቀበሌ 08 ጀምሮ ለሚሰራው መንገድ ጨረታውን ለአሸነፈው ተቋራጭ ቅድሚያ ክፍያ ሲፈፀም አሳማኝ ማሰረጃ ሳይኖር የተከፈለ፣ ብር 55,749.34 የቀበሌ መንገድ ለማሰራት ለዶዘር፣ለግሊደር እና ለሎቬድ ኪራይ ለተፈፀመ ክፍያ ዝቅተና ዋጋ ያቀረበ ተጨራች እያለ ከፍተና ዋጋ ካቀረበ ድርጅት ኢኮኖሚዋ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

- **የደብረ ብርሃን እንጨት ማቀነባበሪያ ኃ/የተ/የግል/ማህበር** ብር 5,988,112.40 በድርጅቱ ግቢ ውስጥ የተገነባው የውስጥ ለውስጥ መንገድ እና የተለያዩ ግንባታዎች በተቋራጭ ሲከናወን ያለጨረታ፣ህጋዊ ባልሆነ የግንባታ ስራ ውል እና ግዥውን እንዲያከናውን ህጋዊ ውክልና በሌለው ስራአስኪያጅ በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ፤ ብር 270,384.72 የውስጥ ለውስጥና የተለያዩ ግንባታዎች ላከናወነው ተቋራጭ ከተፈፀመ ክፍያ ተሰልቶ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ብር 2,187,528.47 በድርጅቱ ግቢ ውስጥ የውስጥ ለውስጥ መንገድ እና የተለያዩ ግንባታዎች ላከናወነ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጸም የእንጨት ማቀነባበሪያ ድርጅት ስራአስኪያጅ ህጋዊ ውክልና ሳይኖራቸው የተከፈለ እና መከፈል ከነበረበታ በላይ በብልጫ ተከፈለ፣ብር 153,528.94 የግቢው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ ለተከናወነብት ሀሰተኛ ውል በማዘጋጀት እና በመዋዋል በአቶ ዩናስ ህንፃ ተቋራጭ እንደሰራ በማስመሰል ያለምንም ውክልና እና ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብ ለድርጅቱ ስራ አስኪያጅ እና ሽሪክ ያለምንም ማስረጃ የተከፈለ፣ ብር 1,401,367.00 በድርጅቱ ተቀጥረው ከሚሰሩ ቻይናውያን ተሰብስቦ ለመንግስት ፈሰስ ልተደረገ ከመቀጠር የሚገኝ የስራ ግብር፣ብር 3,373,421.98 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጭ ፀድቀው የተገኙ የተለያዩ ዕቃዎች፣ብር 609,218.31 ለተለያዩ አካለት ያለምንም ማስረጃ በወጭ ፀድቆ የተከፈለ ሂሳብ፣ብር 866,840.73 ያለግባብ የተከፈለ የምግብና ምቹ ያለሆነ የስራ ቦታ አበል፣በድጋሜ የተከፈለ የደመወዝ ክፊያ እና የተለያዩ እቃዎች ተገዝተው በብልጫ ተከፈለ ክፍያ፤ብር 198,400 የስሚንቶው አይነት ባልተገለፀበት ብዛት 800 ኩንታል ስሚንቶ እንዲገዛ ም/ስራ አስኪያጅ በማዘዝ ሴሪያል ቁጥር እና ቀን በሌለው ነጭ ወረቀት /የንብረት ገቢ ደረሰኝ/የንብረት ሰራተኛዋ /የም/ስራስኪያጅ ልጅ/ ተረክቤአለሁ በማለት ለድርጅቱ ገቢ እንደሆነ በማስመሰል ለግል ጥቅም የዋለ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም ፡፡
- **የደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር 204,273.00** ከንብረት ክፍል ወጭ ያልሆነን የፎቶ ኮፒ ወረቀት ወጭ እንደሆነ በማስመሰል በንብረት ወጭ ደረሰኝ /ሞዴል 22/ ወጭ ከተደረገው ወረቀት ብዛት በኂላ ቁጥር በመጨመር በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም የዋለ፤ ብር 91,253.63 የተለያዩ ንብረቶችን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ማድረጋቸውን ንብረት ክፍል ሰራተኛው ከፈረመ በኂላ ገቢ ያደረጉ ግለሰቦች ከሄዱ በኂላ የንብረት ገቢ ደረሰኝ /በራውንና ኮፒውን/ በማያያዝ ተሰርዟል በማለት ከንብረት ክፍል አውጥቶ ለግል ጥቅም የዋለ፤ብር 227,624.52 ተገዝቶ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሳይረደረግ እና አየር በአየር ወጭ ተደርገው ለግል ጥቅም የዋሉ የተለያዩ ንብረቶች፤ብር43,805.50 በንብረት ወጭ ደረሰኝ ወጭ ተደርገው ለግለሰብ ጥቅም የዋሉ ብሬከሮች እና የኤሌክትሪክ ገመድ፣ብር 169,553.00 ለኮሌጁ አገልግሎት በግዥና በስጦታ የተገኙ የመኪና ጎማ ወጭ በማድረግ ለተሽከርካሪዎች ሳይገጠም ለሹፌር ጥቅም የዋለ፤ብር 48774.00 ከኮምፒውተሮች ላይ ሲስተም ዩኒት በማጉደል በአይሲቲ ማዕከል ባለሙያ ለግል ጥቅም የዋለ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጦ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም ፡፡
- **የጉባላፍቶ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት** ብር 19,395.25 የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ንብረት የሆነች ተሽከርካር አማ 4-01882 ለስራ በተለያዩ ቦታዎች ለተንቀሳቀሰበት ነዳጅ ሲሞላ ከኖርማላይዜሽን ተመን በላይ በሹፌሩ ተሞልቶ ለግል ጥቅም የዋለ

### 1.8.2 ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,758,527.25 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡

ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተከፈለዉ ደግሞ ታክሱ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ የሚያስገድድ የመቆጣጣሪያ ስልት ስለማይኖረው ምን ጊዜም ሊሰበሰብ ስለማይችል አፈፃፀሙ የመግስትን ገንዘብ በማጭበርበር ከተጠቃሚው (ከከፋዩ) በመንግስት ስም ሰብስቦ ለግል ጥቅም በማዋል እንዲሁም በሌሎች ዜጎች ላይ ኢፍታዊ የገበያ ውድድር በመፍጠር በደል የሚደርስ በመሆኑ ላለፈው ትኩረት በመስጠት እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

### 1.8.3. አላፅባብ □ዙ□ናመ □ኢ□፤

ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ154 (74.75%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 13917929.12 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ □ር□ር ሁነታ□ውም□እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**ሠንጠረዥ 9 አላፅባብ □ዙ□ናመ □ኢ□፤**

| ተ.ቁ | አዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2006 ሂሣብ | | | 2007 ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 67 | 18,586,971.52 | 0.78 | 31 | 3526359.35 | |
| 2 | ባሕር ዳር ከተማ | 2 | 13,142.22 | 0.00 | 1 | 2320.00 | |
| 3 | ምክ/ቶጰም | 13 | 503,358.17 | 0.02 | 12 | 2028843.00 | |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | 14 | 414,076.26 | 0.01 | 10 | 264028.50 | |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 19 | 566,103.04 | 0.02 | 17 | 2412772.88 | |
| 6 | □ቡብ ጎንደር | 10 | 1,513,330.83 | 0.06 | 13 | 1205967.77 | |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 7 | 399,651.01 | 0.01 | 12 | 737820.33 | |
| 8 | □ቡብ □ሎ | 10 | 424423.52 | 0.01 | 18 | 778377.23 | |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 24 | 450,819.23 | 0.01 | 19 | 1013018.38 | |
| 10 | አዊ ብሔረሰብ | 4 | 65,633.02 | 0.00 | 10 | 792013.48 | |
| 11 | ኸፀ□ምራብሔረሰብ | 6 | 724,432 | 0.03 | 5 | 410106.62 | |
| 12 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 1 | 4553 | 0.00 | 6 | 746301.58 | |
| | ትምር | 177 | 23,666,493.82 | 1 | 154 | 13917929.12 | |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በዞኖች ደረጃ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 100,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- ***ጤና ጥበቃ ቢሮ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ*** ብር 1,007,070.21 በሰሜን ወሎ ዞን ወልድያ ከተማ አስተዳደር እየተገነባ ላለው የእናቶችና ህፃናት ሆስፒታል 3ተኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ
- ***ገጠር መንገድ ባለስልጣን የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ*** ብር 100,793.86 ከተሰራው የግንባታ ስራ በላይ እና በድጋሚ የተከፈለ ውሎ አበል
- ***ግብርና ቢሮ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ*** ብር 752,961.31 የውሃ ጉድጓድ በአማራ ውሃ ቁፋሮ ድርጅት ሲያስቆፍር ከተያዘው ውል በላይ በብልጫ የተከፈለ
- ***ትምህርት ቢሮ ብር 409,588.62*** የፕላዝማ ጥገና የተሰራበት፣የተለያዩ ግንባታዎች የተከናወኑበት በብልጫ የተከፈለ እና በመደበኛ ስራ ቦታቸው ለተገኙ ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ የውሎና የስልጠና አበል
- ***ጤና ጥበቃ ቢሮ*** ብር 644,142.24 የተለያዩ ግንባታዎች ወጭ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ
- ***ቡሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 188,735.00 አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፣የግንባታ ተጨማሪ የስራ ዝርዝር በተቋራጩ ሳይቀርብ፣በማህበረሰብ ተሳትፎ የተሰራን ስራ በተቋራጩ እንደተሰራ በማድረግ የተከፈለ እና በመድህን ድርጅት መሸን የሚገባውን የተሽከርካሪ ጥገና ወጭ አላግባብ በመ/ቤቱ እንዲሸፈን የተደረገ
- ***ይልማናና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 134,245.31 ሰልጣኞች በሚኖሩበት ቦታ ለተሰጠ ስልጠና አላግባብ እና በብልጫ የተከፈለ ውሎና የስልጠና አበል
- ***ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 136,725.50 አላግባብ በብልጫ የተከፈለ የውሎና የስልጠና አበል
- ***አዴት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 511,752.77 አላግባብ የተከፈለ የኮብል እስቶን ጠረባ፣ምንጣፍ እና የማበረታቻ ክፍያ
- ***ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 156,098.18 የጥራሂና ት/ቤት ግንባታ 2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣አላግባብ የተከፈለ ውሎና ስልጠና አበል እና የኤሌክትሮኒክ እቃዎች ግዥ ሲፈፀም በሎት ግዥ መፈፀም ሲገባው በጥቅል በመካሄዱ ከፍተኛ ዋጋ ከአቀረበ አቅራቢ የተፈፀመ
- ***ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 788,974.48 ከመመሪያ ውጭ አላግባብ የተደረገ ድጋፍ እና በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበልና ስልጠና አበል
- ***ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 125,141.17 በብልጫ የተከፈለ የዕጅ ጉድጓድ ግንባታ እና ውሎ አበልና ስልጠና
- ***አዲአርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 235,806.13 አላግባብ የተከፈለ ውሎ፣ስልጠና እና የበረሃ አበል
- ***ጭልጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 123,575.78 ከታዘዘው በላይ ተከፍሎ የተገኘ የመስተንግዶ ወጭ እና አላግባብ የተከፈለ ውሎ አብል
- ***መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 617,229.94 የአስተዳደሩ የቢሮ ግንባታ ከ1ኛ-3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከማስረጃ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና የስልጠና አበል
- ***ደጋ ዳሞት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ብር 985,920.02 የአስተዳደር ቢሮ ግንባታ ሲከናወን ከውለታ በላይ ተከፍሎ የተገኘ

- **ነፋስ መውጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 261,098.95 ለዲች ቦይ ግንባታ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ፣የመንገድ ስራ ሲከናወን ቅ/ክፍያ ሳይሰበሰብ የቀረና አላግባብ የተከፈለ የውሎና የስልጠና አበል፤
- **ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 692,130.00 የኮብል እስቶን ንጣፍ ሲከናወን ላልተሰራ ስራ የተከፈለ እና በድጋሜ ፀድቆ የተገኘ ወጭ
- **ጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 137,846.67 ለንፁህ መጠጥ ውሃ ግንባታ ግብዓት ሲገዛ በብልጫ የፀደቀ፣ለአዲስ አለም ቀ.3 ጎጥ የንፁህ ውሃ መጠጥ ግንባታ ስራው ሳይጠናቀቅ የተከፈለ ፣አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣የተለያዩ ግዥዎች ሲከናወኑ ከፍተኛ ዋጋ ከአቀረበ አቅራቢ የተፈፀመ
- **እንጅባራ ከተማ አስ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 369,942.18 በተለያዩ ሳይቶች ለተሰሩ የኮብል መንገዶች የውሃ ማፋሰሻ ቦይ ግንባታ ከተሰራው ስራ በላይ የተከፈለ
- **ደጀን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 105,497.385 ትምህርት ጽ/ቤት በደጀን ከተማ እያስገነባ ላለው የአዳራሽ የ4ኛ ዙር ክፍያ ከተሰራው ስራ በላይ የተፈፀመ
- **የኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 110,154.33 ለአስተዳደር ጽ/ቤቱ የባህል አዳራሽ ግንባታ የኤሌክትሮኒክስ ኢንስታሌሽን፣ቀለም ቅብ፣ የወንበርና የመስኮት እድሳትና ጥገና ክፍያ ሲፈጽም በብልጫ ለተቋራጩ የተከፈለ
- **ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 107,065.90 መስክ ለተወጣ ስራ እና ለስብሰባ ክፍያ ሲፈጸም አለአግባብ የተከፈለ የውሎ እና የአልጋ አበል
- **ደብረ ብርሃን ሆስፒታል** ብር 134,475.67 መስክ ለተወጣ ስራ ክፍያ ሲፈጽም አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና ለሰራተኞች የደንብ ልብስ ግዥ ሲፈጸም ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥው መፈፀም ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው አቅራቢ በመፈጸሙ በብልጫ የተከፈለ
- **ደብረ ብርሃን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 247,974.87 ግዥ ሲያከናውን ከተቀዳ ነዳጅ በላይ የተከፈለ ሂሳብ፣ ለ08 ቀበሌ መንገድ ግንባታ፣ለ04 ቀበሌ ወጣት ማዕከል፣ለጠባሴ መድሃኒያለም ትምህርት ቤት ሴፍቲታንከር ግንባታ የተለያዩ ዙሮች ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተፈፀመ
- **ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 182,994.29 የተለያዩ እቃዎች እና ለትምህርት ቤት ግንባታ እንጨት ግዥ ሲፈጸም ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ፣የቢራ ቀበሌ የመስኖ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተፈጸመ እና አለአግባብ የተፈጸመ ውሎ አበል
- **በረኸት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 114,679.53 መተህ ብላ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የብሎክ ግንባታ ሲያከናውን በብልጫ የተከፈለ፣አለአግባብ የተፈፀመ የውሎና የአልጋ አበል እንዲሁም ለኮንትራት ሰራተኞች አለአግባብ የተፈፀመ የደመወዝ ወጭ፤
- **ወረባቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 114,833.85 ክፍያ ሲፈጸም አላግባብ የተፈፀመ የውሎና የስልጠና አበል፤
- **ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 208,851.00 የመንገድ ጠረጋ ሲያከናውን በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተፈጸመ እና አለአግባብ የተፈፀመ ውሎ አበል ክፍያ

- **ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 475,411.02 የፋብሪካ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም በብልጫ የተፈጸመ፣ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበልና የቢሮ ግንባታ ሲከናወን እስከ መጨረሻ ዙር ያልተሰበሰበ ማቴሪያል ኦን ሳይት፤
- **ሳህላ ሰየምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 383,274.17 ለተለያዩ መ/ቤቶች ግንባታ የቆርቆሮ ግዥ ሲያከናውን ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ፣ነዳጅ ለማጓጓዝ ለመኪና ኪራይ የተጋነነ ዋጋ የተከፈለ፣ አላግባብ የተፈጸመ የደመወዝ፣ስልጠና እና የፈተና ምዘና ወጭ፣በባለሙያ አስፈላጊነቱ ሳይረጋገጥ የተገዛ የሞተር እና ዲፈረንሻል ግዥ እንዲሁም አለአግባብ የተፈጸመ ውሎ አበል፤
- **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 155,556.34 የውሃ ምንጭ ግንባታ ክፍያ ለአርቲዥያን ሲፈፀም በብልጫ የተፈፀመ እና አለአግባብ የተፈፀመ የውሎ እና የስልጠና አበል፤
- **ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 189,137.27 ለፖሊስ ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ሲያከናውን ከውለታ በላይ የስራ ዝርዝር ሳይኖር የተከፈለ እና በብልጫ የተከፈለ፤
- **ቦሩ ሜዳ ሆስፒታል ብር 125,549.91** ሲያከናውን መድሃኒት፣ህክምና ዕቃዎች እና የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲከናወን ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈጸመ እንዲሁም አለአግባብ የተፈጸመ ውሎ አበል፤
- **ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 100,698.50 የቦታ ካሳ ክፍያ ሲፈፀም ለባለይዞታው መከፈል ሲገባው አለአግባብ ለሌላ ሰው የተከፈለ፣አለአግባብ የተፈጸመ ውሎ አበልና የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ

የ2007 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2006 በጀት ዓመት ብር 23,666,493.82 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ23 ሲቀንስ በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 9,748,564.70 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 762,049.81 (5.48%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ብር 13,155,879.31 ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

### 1.8.5 የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ44 (21.35%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 45,059,727.70 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች ግብርና ቢሮ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ ብር 5,612,018.63 በመራዊ ከተማ የቀዝቃዛ መጋዘን ግንባታ ሲከናወን ያለውል ስምምነት የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ፣ትምህርት ቢሮ ብር 5,329,562.99 የግንባታ ስፍር ልኬታ ሳይቀርብ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ፣ፍኖተ-ሠላም ከተማ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 2,435,886.98 የኮብል እስቶን ምንጣፍ እና አዲስ ጠጠር ምንጣፍ ለማሰራት ውል የቴዘ ሲሆን ስራው ሳይጠናቀቅ እና ማስረጃው ሳይሟላ በወጭ የፀደቀ፣ታች ጋይንት ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 1,393,586.57 ለአስተዳደሩ የቢሮ ግንባታ የመጀመሪያና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የግንባታ ስራ ልኬት ሳይቀርብ የተከፈለ፣ እብናት ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል

ብር 1,012,965.89 ለመጣቶች መዝናኛ ማዕከል አዳራሽ ግንባታ ሲከናወን በባለሙያ ቅድመ የስራ እና የዋጋ ዝርዝር ሳይቀርብ እና የዕጅ ጉድጓድ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ጊዜያዊ ርክክብ ሳይደረግ የተፈጸመ ክፍያ፣ ወልድያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 13,420,024.50 የግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ከመፈፀሙ በፊት የስራ ዝርዝር፣የስራ ልኬት ማስረጃ ሳይቀርብ እና በመሃንዲስ የተረጋገጠ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅ ያልተፈጸመ ክፍያ፣ባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 1,455,787.27 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲገነባ በተቋራጩ የስራ ልኬት ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣ለጋንቦ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 2,384,550.85 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲያከናውን የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣ከምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 1,354,358.59 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲያከናውን የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣ ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,852,063.00 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲያከናውን የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፤

እነዚህ ከአንድ ሚሊየን ብር በላይ ሂሣብ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

**1.8.6 ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፤**

ማንኛውም □አ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባ ይህን በመተላለአ በ87 (42.23%)መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር **24,831,883.94** የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ-10 ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፣

| ተ.ቀ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2006 ሂሣብ | | | 2007 ሂሣብ | | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 30 | 2,085,953.07 | 0.08 | 11 | 2,225,308.32 | |
| 2 | ባህር ዳር | 3 | 645,226.19 | | | | |
| 2 | ምክ/□ጎም | 7 | 2,195,965.71 | 0.09 | 7 | 1326397.48 | |
| 3 | ምሥ/□ጎም | 10 | 2,492,346.11 | 0.10 | 10 | 969242.88 | |
| 4 | ሰሜን ጎንደር | 14 | 2,525,636.19 | 0.09 | 13 | 2082717.70 | |
| 5 | ደቡብ ጎንደር | 7 | 3,113,576.54 | 0.13 | 8 | 1468924.35 | |
| 6 | አዊ ብሔረሰብ | 2 | 24,171.73 | 0.00 | 2 | 387614.00 | |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 5 | 57,698.54 | 0.00 | 5 | 4891274.58 | |
| 8 | □ቡብ □ሎ | 7 | 9,972,489.23 | 0.42 | 13 | 3750221.43 | |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 10 | 1,140,082.63 | 0.04 | 12 | 5267486.80 | |
| 10 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | - | | 0 | 5 | 2130437.40 | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ዋግኽምራ | 2 | 155,862.69 | 0.00 | 2 | 332259.00 | |
| | ትምር | 97 | 24409008.63 | 0.95 | 88 | 24831883.94 | 0 |

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 24,409,008.63 ጋር ሲነፃፀር በ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ9 ቀንሶ□እና በገንዘብ መጠን ብር 422,875.31 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ያለው ችግር በተመሳሳይ ሁኔታ መሄዱን ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ችግር ቀላል ሥላልሆነ በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚያመለክት ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 1.8.7. ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፣

ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ34(6%) መ/ቤቶች ብር 55,072,281.07 የተገኘ ሲሆን ከመ/ቤቶች መካከልም ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 588,422.62፣ ቋሪት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 321,035.81፣ደጀን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 248,144.57፣ አዲአርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 546,137.53፣መስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 9,474,009.80፣ ጣቁሳ ወወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,967,664.25፣ አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,165,514.58፣ ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብ 303,229.33፣ ጃናሞራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 919,612.50፣ ሊቦከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 244,821.68፣ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 9,804,578.82፣ለገሂዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 233,164.57፣ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,861,927.65፣ ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,353,673.81፣ ወልድያ ከተማ አስ/ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 9,413,365.26፣ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,281,091.12፣ኤፍራታ ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,110,096.35፣ሸዋሮቢት ከተማ አስ/ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 687,968.37፣ ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 214,848.67፣ መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 336,678.65፣ ባቲ ከተማ አስ/ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,283,499.51፣ አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 500,871.14፣ ጁሌጥሙጋ 547,107.00 በድምሩ ብር 54,407,463.59፣ ከ200 ሽህ ብር በላይ የያዙ የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃው ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻሉ የወጪዎቹን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ይሁንና ስለተወሰደው እርምጃ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

### 1.8.8 የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሣብ፤

□ክቃዎችናአገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለ□ □ዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃናም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ

ኦዲት ሲደረግ በ166 (80.58%) መ/ቤቶች ብር 126,923,643.06 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል። □ር□ሩም ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ 11 የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ፣**

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2006 ሂሣብ | | | 2007 ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | □መ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1. | የክልል መ/ቤቶች | 103 | 27,233,637.13 | 29 | 38 | 13,515,315.20 | |
| 2. | ባህርዳር | 2 | 220,636.31 | 0.00 | | | |
| 3. | ምክ/□ጽም | 11 | 14504238.22 | 0.15 | 14 | 8,851,674.50 | |
| 4. | ምሥ/□ጽም | 17 | 8638045.66 | 0.09 | 17 | 12,145,339.69 | |
| 5. | ሰሜን ጎንደር | 19 | 8472,791.12 | 0.08 | 16 | 10897750.69 | |
| 6. | ደቡብ ጎንደር | 10 | 6,276,993.27 | 0.06 | 12 | 21,190,741.36 | |
| 7. | አዊ ብሔረሰብ | 5 | 621491.16 | 0.00 | 6 | 12355627.92 | |
| 8. | ሰሜን ወሎ | 7 | 3126007.83 | 0.03 | 12 | 6986735.39 | |
| 9. | □ቡብ □ሎ | 14 | 14301775.14 | 0.14 | 16 | 13250876.03 | |
| 10. | ሰሜን ሸዋ | 25 | 6,100,914.26 | 0.06 | 24 | 19804447.22 | |
| 11. | ኸፀ□ምራ ብሔረሰብ | 4 | 1,034,416.23 | 0.01 | 5 | 2569408.36 | |
| 12. | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 2 | 4,972,097.68 | 0.05 | 6 | 5355726.70 | |
| | ትምር | 219 | 95,503,044.1 | | 166 | 126,923,643.06 | |

ሠንጠረዡ እን□ሚ□መለ□ተ□ የግዥ አፈጻፀም ጉድለት ጎልቶ የሚታይባቸው መ/ቤቶች፡-

- ደቡብ ጎንደር ዞን ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 15,764,772.60 ለመምሪያው ሴክተር መ/ቤት ህንፃ ግንባታ ያለግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣አለፋ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,606,923.31 የሻውራ ወረዳ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የአጥር ግንባታ እና የተለያዩ እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሲፈፀም ያለግልጽ ጨረታ እና የታደሰ ንግድ ፈቃድ ካላቀረበ አቅራቢ የተፈፀመ፣ጃቢጠህናን ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,809,311.97 የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ፣የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ እና በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ወቅት ከፍተኛ ግዥ የተፈፀመ፣ሜጫ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,961,388.20 የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ እና የፖስታው የመክፈቻ ቀን ሳይደርስ ከመመሪያው ውጭ በመክፈት የተከናወነ፣አዊ ብሔረሰብ አስ/ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 9,202,098.09 የውሃ ተቋማት ግንባታ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 3,186,981.22 ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ እና የግዥ ጥያቄ/የስራ ትዕዛዝ/ ሳይቀርብ የተፈፀመ፣ቀወት ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,584,342.98 ግዥ ሲፈጸም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣

  በረኸት ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 6,414,531.20 የተለያዩ ዕቃዎች እና የዶዘር ኪራይ ግዥ ሲፈፀም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣አምባሰል ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,759,161.67 ግዥ ሲፈፅም አሳማኝ ምክንያት ሳቀርብ በቀጥታ፣በፕሮፎርማ እና በውስን ጨረታ የተፈፀመ፣ለጋንቦ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,875,147.88 ግዥ ሲፈፅም ያልግልጽ ጨረታ እና ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ፣ከለላ ወረዳ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,832,472.97 ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ፣ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ፣ በውስን ጨረታ፣በቀጥታ ግዥ እና የተገዛው ዕቃ የንብረት ደረሰኝ ሳቀርብለት የተገኘ፣መገኘቱ ዋና ዋናዎቹና

ከ1,600,000.00 ብር በላይ ግኝት የተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የዕቃ ግዥ መመሪያ በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 95,503,044.10 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ53 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን በብር 31,420,598.96 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል ግዥ እየፈፀሙ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)

**1.9 . የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤**

**1.9.1 ተቀጽላ ሌጀር ያልዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ49 መ/ቤቶች ብር 64,188,419.24 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቼ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መለልስ እንደተረጋገጠው ብር 1,636,812.48 ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ሲሆን ቀሪው ብር 62,551,606.76 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 14/2008 ዓ.ም ድረስ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

**ሠንጠረዥ 12 ተቀጽላ ሌጀር ያልዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

| ተ.ቁ. | መ/ቤት ስም | የመ/ቤቱ ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 16 | 29,416,262.91 | 45.83 |
| 2 | ምዕራብ ጎጃም | 1 | 5,528,772.16 | 8.61 |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | 10 | 5,367,723.86 | 8.36 |
| 4 | ሰሜን ጎንደር | 9 | 7,864,111.59 | 12.25 |
| 5 | ደቡብ ጎንደር | 5 | 1,155,868.11 | 1.8 |
| 6 | አዊ ብሔረሰብ | | 0 | 0 |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 1 | 2,898,737.66 | 4.52 |
| 8 | ደቡብ ወሎ | 1 | 3,543,423.28 | 5.52 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 6 | 8,413,519.67 | 13.11 |
| 10 | ዋግኽምራ | | 0 | 0 |
| 11 | ኦሮሞ ብሄረሰብ | | 0 | 0 |
| 12 | ባ/ደር | | 0 | 0 |
| | **ድምር** | **49** | **64,188,419.24** | **1.00** |

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ፣ የክልል ተጠሪ መ/ቤቶችና ቢሮዎች፣ሰሜን ሸዋ ዞን፣ሰሜን ጎንደር ዞን፣ምስራቅ ጎጃም ዞን እና ምዕራብ ጎጃም በቅደም ተከተል ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቼ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ መሠራት እንዳለበት በሪፖርታችን ያሳሰብን ቢሆንም ስለተወሰደው

የማስተካከያ እርምጃ የደረሰን ምላሽ ባለመኖሩ ለምን ያህሉ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር እንደተዘጋጀ ማወቅ አልተቻለም፡፡

1.11. የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት በትክክል የተዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ልዩነቶች ተገኝተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 15 የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

| በማነስ/በ ብልጫ | ጥሬ ገንዘብ | ባንክ ሂሳብ | የገቢ ሂሳብ | የተሰብሳቢ ሂሳብ | የወጪ ሂሳብ | የተከፋይ ሂሳብ | የተጣራ ሀብት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በማነስ | | 119,597.43 | 73,474.37 | 4,937,889.28 | 1,227,453.31 | 440,980.15 | 931,203.42 |
| በመብለጥ | | 243,485.12 | 34,358.15 | 1,229,761.31 | 5,181,374.40 | 474,687.41 | 0 |

የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በአመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶቻቸው ላይ በየሂሳብ ዓይነቱ አላግባብ በማነሰና በመብለጥ ሪፖርት የተደረጉ ሂሳቦች ተገኝተዋል፡፡ ይህም የክልሉንም ሆነ የአገሪቱን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ በተገለጹት ሂሳቦች የገንዘብ መጠን በማዛባት ለውሣኔ ሰጪ አካላት የተሳሳተ መረጃ ሊሰጥ እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ማስተካከያው በየደረጃው ተደርጎ የተዛባው ሂሳብ እንዲስተካከል በየኦዲት ሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመለከቱ)

1.12 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፣

1.12.1 የንብረት ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 206 መ/ቤቶች መካከል በ106 (51.46%)መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ንብረትን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ላለመቻሉ ምክንያቶች፤

- አላቂና ቋሚ ዕቃዎች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ እየተቆጠሩ (ከFAR; UC እና BIN card) ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከሩ መሆኑ፣
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (የእቃ መቆጣጠሪያ ካርዶች) ባለመቋቋሙ እና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማይደረግ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም፤

- በንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረቶች ለቆጠራ አመቺ በሆነ መልኩ በባህሪ፤በአድሜና በአገልግሎት አይነት ለይቶ አለማስቀመጥ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ በቆጠራ የሚገኘውን ብቻ ቆጥሮ ለተተኪዎች ከማስረከብ ውጭ እንደመመሪያዉ ማስረከብ የሚገባቸውን ያህል ስለመሆኑ በውስጥ ኦዲተሮች በኦዲት ከተረጋገጠ በኃላ አለመሆኑ፤
- ብረትን ከመጋዘን ከወጣ በኋላም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ሃብት መሆኑ ታውቆ አለመከታተል የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች የየወሩ ከወጪ ቀሪ በመመሪያዉ መሰረት የሒሳብ ሪፖርት አካል እንዲሆኑ አለመደረጉ የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤ አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 መመልከት ይቻላል)

**የንብረት ሂሳብ ጉድለት ብር 270,635.26**

- ቦረና አጠ/ደ/መስናዶ 2ኛ ደ/ት/ቤት ብር 19,146.00 የትምህርት ቤቱ የንብረት ሰራተኛ ስራ ከጀመሩበት ከ02/3/2002 እስከ መስከረም/2006 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- በሳይንት ወረዳ የአምባ ፈሪት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 42,922.11 የጤና አጠባበቅ ጣቢያው ንብረት ሰራተኛ /ፋርማሲ ቴክኒሽያን/ የሆኑት ከ27/10/2004 እስከ 14/09/2006 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የመድሃኒት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- ደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር 208,567.15 ንብረት ክፍል ሰራተኛው ከ2000 ዓ.ም እስከ 30/10/2007 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣ ሲሆን የሚመለከታቸው የፍትህ አካላት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## ምዕራፍ 2:- ያለፉት አምስት □መታት አፈፃፀም

### 2.1 የዕቅድ አፈፃፀም ከ2003 - 2007 ሂሳብ በጀት ዓመታት

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው ተግባርና □ሃላፊነት መሠረት ካለው የሰው □ሃ□ል □ር □ተ□□መ የሥራ መርሃ ግብር በማውጣት ከ2003□እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ ያለው የ5 ዓመት ክቅት ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ-1፡- የአምስት አመት □ክቅት ክንውን በአወቃቀር እርከን፤**

| ዓ/ም | በክልል (ማዕከል) | | በዞን | | ከተማ አስተ | | በወረዳ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕቅድ | ክንውን | ዕቅድ | ክንውን | ዕቅድ | ክንዉን | ዕቅድ | ክንውን | ዕቅድ | ክንውን |
| 2003 | 39 | 36 | 2 | 2 | 20 | 20 | 91 | 91 | 152 | 149 |
| 2004 | 25 | 27 | 2 | 2 | 14 | 16 | 78 | 80 | 119 | 125 |
| 2005 | 34 | 34 | 8 | 8 | 30 | 30 | 105 | 91 | 177 | 163 |
| 2006 | 187 | 165 | 3 | 3 | 32 | 32 | 169 | 168 | 391 | 368 |
| 2007 | 76 | 70 | 9 | 9 | 31 | 31 | 143 | 139 | 259 | 249 |
| **ድምር** | **361** | **332** | **24** | **24** | **127** | **129** | **586** | **569** | **1098** | **1054** |

1. ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የክልሉ የኦዲት ክንውን የ2003 ሂሳብ በጀት ዓመት በቁጥር የ149 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት የነበረ ሲሆን የ2007 ሂሳብ በጀት ዓመት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ጨምሮ የ249 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በ2007 ሂሳብ በጀት ዓመት የኦዲት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ካሉት 442 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 56.33% የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ ደግሞ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የበጀት ወጪ ብር 17,130,995,857.81 በመሆኑ በ2007 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው ብር 21,526,627,543 አኳያ ሲታይ 79.6% የኦዲት ሽፋን ላይ እንደተደረሰ መረጃው ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በዓምስቱ □መታት የ1098 መ/ቤቶች ኦዲት ለማድረግ ታቅ□ 1054 /96%/ ተከናውኗል፡፡ ይህም በክልሉ ከሚገኙ 442 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋር ሲነፃፀር በ5 ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በ2.38 በድግግሞሽ ከ2 እስከ 3 ጊዜ በኦዲት መሸፈናቸውን ያመለክታል፡፡

መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው በመለዋወጡና በመጨመሩ ምክንያት በታሰበው መሠረት በቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎች፤ የአካል ተሃድሶ ማዕከላት፡ በወረዳ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች፤ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን ከዚህ በፊት በም/ቤቱ የተሰጠው አቅጣጫ ተግባራዊ እንዲሆን

አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡ ይህ ተግባራዊ ቢደረግ ሁሉም ኦዲት ተደራጊ ተቀማት በየበጀት ዓመቱ የኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ ያደረጋል፡፡

## 2.2 ከ2003 -2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፤

ከ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ጀምሮ ባሉት 5 ዓመታት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች በተገኙ መረጃዎች መሠረት የዋናዋና ግኝቶች አማካይ ስሌት (Weighted Average) ተሠርቶየሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡


| ተ.ቁ | የኦዲት ግኝት | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | ድምር | አማካኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥሬ ገንዘብ ጉድለት | 2,224,173.79 | 709,701.20 | 86,480.14 | 392,896.67 | 3179036.91 | 6,592,288.71 | 1,318,457.74 |
| 2 | የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የገቢ ሂሣብ | 155,947.55 | 86,367.58 | 191,160.38 | 0 | 0 | 433,475.51 | 86,695.10 |
| 3 | የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጭ ሂሣብ | 251,478.15 | 3,450,722.75 | 1,292,111.10 | 14,483,471.30 | 20738029.49 | 40,215,812.79 | 8,043,162.55 |
| 4 | ለግል ጥቅም የዋለ | 0 | 215,456.60 | 66,568.94 | 8,789.19 | 14560.53 | 305,375.26 | 61,075.05 |
| 5 | አላግባብ የተከፈለ | 9,969,278.59 | 2,210,813.01 | 8,628,883.49 | 23,666,493.82 | 13917929.12 | 58,393,398.03 | 11,678,679.60 |
| 6 | ስርዓቱን ባልተ ከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ወጪ | 10,527,600.49 | 41,408,198.12 | 19,007,315.58 | 21,662,955.93 | 45059727.7 | 137,665,797.82 | 27,533,159.56 |
| 7 | የግዥ ስርዓቱን ያልተከተለ | 51,688,476.03 | 289,013,714.62 | 107,343,734.23 | 95,503,044.01 | 126923643.1 | 670,472,611.95 | 134,094,522.39 |
| 8 | ማስረጃ ያልቀረበበት | 4,894,887.89 | 0 | 13,845,728.41 | 24,409,008.63 | 24831883.94 | 67,981,508.87 | 13,596,301.77 |
| 9 | ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ | 3,349,953.18 | 2,620,727.62 | 13,845,728.41 | 32,397,874.07 | 55072281.07 | 107,286,564.35 | 21,457,312.87 |
| | ድምር | 83,061,795.67 | 339,715,701.50 | 164,307,710.68 | 212,524,533.62 | 289,737,091.82 | 1,089,346,833.29 | 217,869,366.63 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ ፋይናንስ አስተዳደር በተዘረዘሩት ዋና ዋና ግኝቶች ድክመት ይታይበታል፡፡ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች እንደየባህሪያቸው ተቀራራቢነት አጠቃላይ አቅጣጫው በሚከተሉት ግራፎች ተመልክቷል፡፡

### የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የሚመራው በአብክመ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003፤ ደንብ ቁጥር 89/2004፤ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2004 እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት የአሰራር ማንዋሎች መሰረት ነው፡፡ ጥሬ ገንዘብ በባህሪው ለተለያዩ ብክነቶችና አደጋዎች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ በመሆኑ በጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መደገፍ ይኖርበታል፡፡ ከውስጥ ቁጥጥር ስርአቶች አፈፃፀም አንፃርም ኦዲት ሲደረግ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በየአመቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህን ኦዲት ለማረጋገጥ ደግሞ የጥሬ ገንዘብ ወጪ በሂሳብ መዝገብ (ሌጀር) ምዝገባ እየተካሄደ በበጀት አመቱ መጨረሻ ደግሞ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና እንደ ጥሬ ገንዘብ

የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላ ህጋዊ ቆጠራ መደረግና መመዛዘን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር መሰረታዊው ችግር ቅድመ ሁኔታዎች ስለማይሟሉ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት የማይቻልባቸው ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየጊዜው ቁጥራቸው ቀላል አለመሆኑ ነው፡፡




- ከሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየባቸዉ የኦዲት ዓመቶች በ2003 ሂሳብ ብር 2,224,173.79 እና በ2007 ሂሳብ ብር 3,179,036.91 በተከታታይ ከአማካኙ ብር 1,318,457.74 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ተገኝተዋል፡፡

በ2007 ሂሳብ በጀት ዓመት የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ጎልቶ ሊታይ የቻለዉ ፤

- በከሚሴ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ብር 1,693,403.721 የኮሌጁ ዋና ገንዘብ ያዥ ስራ ከጀመሩበት ከ18/01/02 እስከ 24/06/2007 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፤

- በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 479,759.20 የባለሙያ እጥረት በመኖሩ አስፈላጊው የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር በትክክል ስለማይሠራ፣ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ስለማይደረግ ለብክነት በር በመክፈቱ ብዙ ገንዘብ ሊባክን ችሏል፡፡


  እንዲሁም በተመሳሳይ ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በ2004 በጀት ዓመት ከ149 መ/ቤቶች ዉስጥ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ጉድለት የተገኘዉ በ12 መ/ቤቶች ብቻ ቢሆንም የ57 መ/ቤቶችን ጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ ወይም የተጣራ ሂሳባቸዉን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የባለሙያ እጥረት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚደረገዉ ጥረት ከሚፈለገዉ ደረጃ ያልደረሰ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡

ከላይ ከተጠቀሰዉ ገንዘብ ዉስጥ በ2003 በጀት ዓመት ብር 409.06 የተተካ፤ በ2004 በጀት ዓመት ብር ብር 47,039.74 የተተካ፤ ብር 1,254,504.20 በፍታብሄርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ ያለ እና ብር 922,629.65 ደግሞ ያለበት ሁኔታ እንደማይታወቅ በወቅቱ ከደረሰን ምላሽ መረዳት ተችሏል፤ በ2005

በጀት ዓመት ብር ብር 7480.55 የተተካ፤ ብር 608,266.84 በፍታብሄርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ ያለ እና ብር 93,953.79 ደግሞ ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ እንደነበር በወቅቱ የደረሰን ምላሽ ያመለክታል፡ ፡ በ2006 በጀት ዓመት ብር 37,377 በ2007 በጀት ዓመት ግን ምላሹ ስላልመጣልን የተተካ መሆኑን ማወቅ አልተቻለም፡፡

**የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ**

የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት ዓላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በስትራቴጂክ ዘመኑ ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ብር 433,475.51 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡




ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በ2003 ሂሳብ ብር 155,947.55 እና በ2005 ሂሳብ ብር 191,160.38 በመጭበርበሩ ከአማካኙ ብር 115,260.34 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በ2005 በጀት ዓመት ከተጭበረበረዉ ሂሳብ ላይ ብር 191,160.38 ላይ ብር **37,377 (19.55%)** ከየሚመለከታቸው ላይ በክትትል የተተካ መሆኑ ታውቋል፡፡

በገቢ ሂሳብ ኦዲት ኦዲት ወቅት የተስተዋሉት ዋና ዋና የማጭበርበር ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡


- የካፒታል ዋጋ እድገት ስሌት ላይ ተገቢ ያልሆኑ ማስረጃዎችን መውሰድና የግብሩን መጠን በስሌት ማሳነስ፤
- የገቢ ደረሰኞችን ከ--እስከ መዝግቦ አለማሰራጨትና የተሰራጩ ደረሰኝ በትክክል ተሰርቶበት ገንዘቡ ለሚመለከተው ገቢ መደረጉ ተረጋግጦ እንዲመለስ የሚደረገው ክትትል አናሳ መሆኑ፣
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ሲፈለጉ አለመቅረብ፤
- የገቢ ደረሰኞችን አበላልጦ ገቢ መሰብሰብና ከትክክለኛው ቁጥር ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግ፤

- የገቢ ደረሰኞች ሲጠፉ ወደ ገንዘብ ቀይሮ ለማስከፈል በወንጀል ይጠየቁ ከማለት ዉጭ በገንዘብ ለዉጦ የፍታብሄር ክስ ለመመስረት የህግ ክፍተት መኖሩ፡
- የውስጥ ገቢ ያላቸው መ/ቤቶች ገቢያቸውን በዕቅድ ይዘው ለሚመለከተው አለማሳወቅና በዚያው መሠረት ስራ ላይ አውለው የሂሳብ ሪፖርት አለማዘጋጀት፤
- ጠቃሚ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶችን በማዳከም ለመንግስት ገንዘብ ብክነት የአሰራር ክፍተት መፍጠር፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ደረሰኝ በስሙ ወጪ ያደርጋል፤ የገቢ ደረሰኝ ራሱ ያዘጋጃል፤ገንዘብ ይሰበስባል፤ሂሳቡን ራሱ መዝግቦ ለሚመለከተው በሙሉ ወይም በከፊል ፈሰስ ያደርጋል፤ በዚህ አሰራር ምክንያት (ቁጥጥር ሳይደረግበት) ሁለት ደረሰኞችን (አንዱ ሕጋዊ ሌላው ሕገ ወጥ) ጎን ለጎን በመጠቀም ገቢ በመሰብሰብ ለግል ጥቅማቸው ማዋል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እነዚህንና ባጠቃላይ የገቢ አሰባሰብ በተለይም የደረሰኞችን ዝውውር (በህጋዊ ርክክብ፤ የደረሰኙን ከ---እስከ እና ሴሪ በመጥቀስ መመዝገብና ስራ ላይ የዋሉትን እየተከታተሉ ማስመለስ)፤ የገቢ አሰባሰብ ታሪፎችንና መመሪያዎችን በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ የመንግስት ገቢን ሰብስቦ ለታቀደለት ዓላማ ለማዋል ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ**


በአምስት ዓመቱ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት ወጪ በድምሩ ብር 40,215,812.79 ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው በግራፍ ቀርቧል፡፡




- ከላይ በግራፍ እንደተመለከተው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ክፍያ የ5 ኣመቱ ሲነጻጸር የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 14,483,471.30 እና በ2007 ብር 20,738,029.49 ከአማካዩ ብር 8,043,162.55 ከፍተኛዉን ድርሻ ይዞ ይታያል፤ ይህ የተከሰተው በአብዛኛው በሰሜን ጉንደር ዞን

በላይ አርማጭሆ ወረዳ በትክል ደንጋይ መሪ ማዘጋጃ ቤት፣ የደብረ ብርሃን እንጨት ማቀነባበሪያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ የአብክመ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡

### ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ




- ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ በ2004 ብር 215,456.60 እና በ2005 ብር 66,568.94 ከአማካዩ ብር 61,075.05 በላይ በመሆኑ ከፍተኛ ብልጫ አለ□፡፡ በመሆኑም በ2004 በርካታ የመንገስት ገንዘብ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ በአጥፊዎች ላይ አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ የዉስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡


### አላግባብ የተከፈለ ክፍያ

አላግባብ የተከፈለ ክፍያ በ5 ዓመቱ ብር 58,393,398.03 ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡




- አላግባብ የተከፈዉ ክፍያ በ2006 በጀት ብር 23,666,493.82 እና በ2007 ብር 13,917,929.12 ከአማካኙ ብር 11,678,679.61 በላይ በመሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም ክፍያዎች አላግባብ የሚፈጸሙ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ**





- ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ በ96 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 93,271,932.81 የተገኘ ሲሆን በተለይ በ2004 በጀት ዓመት ብር 41,408,198.12 እና በ2007 ብር 45,059,727.70 ከአማካኙ ብር 27,533,159.56 በመብለጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡

**□ፅዴ ሥር□ቱን ያልጠበቀ የፅዴ**




- □ፅዴ ሥር□ቱን ያልጠበቀ የፅዴ በመ□ናም በ2004 ብር 289,013,714.62 እና በ2007 ብር 126,923,643.10 ከአማካዩ ብር *134,094,522.39* በላይ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ ይህም የግዥ ሥርዓቱን አለመጠበቅና ችግሩ አለመሻሻሉን ያሳያል፡፡

**ማስረጃ ያልቀረበለት ማ□ቸ**




- ማስረጃ ያልቀረበለት ማ□ቸ በ2006 ብር 24,409,008.63 በ2007 ብር 24,831,883.94 ከአማካዩ ብር 13,596,301.77 ከፍተኛ ብልጫ አለ□፡፡ በመሆኑም በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመት የመንግስት ገንዘብ ያለበቂና አስተማማኝ ማስረጃ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ**



ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ በ2006 ብር 32,397,874.07 እና በ2007 ብር 55,072,281.07 ከአማካኙ ብር 21,457,312.87 በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ያሳያሉ፡፡

- ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ በ2007 በጀት ዓመት ብር 32,397,874.07 እና የ2007 ብር 55,072,281.07 ከአማካኙ ብር 21,457,312.87 ከፍተኛዉን ድርሻ ይዞ ይታያል፤ ይህም ማስረጃዎችን በአግባባ ይዞ ለኦዲት ስራ ሲፈለጉ በማቅረብ በኩል ክፍተት መኖሩንና በትክክል ለመንግስት ስራ የተፈጸሙ ክፍያዎች መሆናቸውን ለማረጋጋጥ አስቸጋሪ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

**በወጪ ሂሳቦች ላይ በአብዛኛው የሚስተዋሉ ዋና ዋና ግኝቶች፡**

- የምግብ ዋስትና የሴፍትኔት ሂሳብ በትክክል ለተጠቃሚዎች አለማድረስና ሀሰተኛ ስም በማካተት፤ በተደጋጋሚ በወጪ በማጸደቅ ገንዘቡን ለግል ጥቅም ማዋል፤
- በክፍያና በንብረት ደረሰኞች ላይ ከፊትና ከኃላ ቁጥር መጨመር፤ ስርዝ ድልዝ ማድረግና ከቀረበ ማስረጃ /ደረሰኝ በላይ ሂሳብ ማወራረድ/
- መስክ ሳይወጣ የውሎ አበል ክፍያ መፈጸም ፤ለአንድ ጊዜ የመስክ ሥራ ከተለያዩ ፕሮጀክቶችና መደበኛ በጀት ሂሣብ ላይ በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ መፈፀም፣ ከዓመቱ ቀናት በላይ በተደጋጋሚ ቀናት አበል መክፈል፤
- በስልጠና የተሳተፉ አባላትን ዝርዝርና አቴንዳንስ ሳይዙ ክፍያ መፈጸምና በስልጠና ያልተሳተፉ ሰዎች ስምን አካቶ መክፈል፤ የመስተንግደሶ ወጪዎችን አስቀድሞ በውድድር የተመረጠ አቅራቢ አለመለየት፤የተሳታፊዎችን ማንነትና የሚገባቸውን መስተንግዶ ዓይነትና መጠን በግልጽና ይህንኑ በሚያሳይ ውሳኔ አለማስደገፍ፤ ለብክነት በር በከፈተ አሰራር መፈጸም፤
- የግንባታ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ ክፍያ መፈጸም፣ በሂሳብስሌት ስህተት ፣ የግንባታ ስራን በትክክኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ አለማስቀመጥና ቀደም ባሉ ዙር ክፍያዎች የተሰራንና ክፍያ የተፈጸመበትን በድጋሚ ማቅረብ፤
- ተገቢውን ስፔስፊኬሽን አዘጋጅቶ ወደ ግዥ አለመግባትና የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ/ንብረት ገዝቶ ገቢ ማድረግ፤(ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ ከነበረም ከዚያ ውጭ መረከብ፤
- አስቀድሞ የተጠቃለለ የግዥ እቅድ አለማዘጋጀት እና የግልጽ ጨረታ ዘዴን የመጀመሪያ ምርጫ አለማድረግ ብሎም የግዥ ዘዴዎችን በተጨባጭ ምክንያት ላይ ተመስርቶ አለመምረጥና የግዥ ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት መዝግቦ/ቃለ ጉባዔ ይዞ ለ3ኛ ወገን በተጨባጭ ማስረጃነት አለማቅረብ፤
- በግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ መገዛት ለሚገባው ግዥ የጨረታ ማስታወቂያ አለማውጣት ቢወጣም በጨረታው በቂ ተወዳደሪ እንዲቀርብ ምቹ ሁኔታ አለመፍጠር፤
- ተገቢ ማስረጃ (የግዥ ጥያቄ፤ የጨረታ ማስታወቂያ፤የተወዳደሪዎች ሰነድ፤ፕሮፎርማ፤ ቃለ ጉባዔ ውሳኔ፤ ለፕሮጀክት ሥራ የክፍያ ሂሣብ ማረጋገጫ (Payment certificate) የንብረት ገቢ ደረሰኝ፤ የውል ሰነዶችን--የመሳሰሉት) ተሟልተውና ተያይዞ ሳይቀርቡ ክፍያ መፈፀም፤


# ምዕራፍ -3:- ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶች፤

## 3.1 የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ!

### ማጠቃለያ፣

1. በዚህ አጭር ሪፖርት የውስጥ ክፍሎች በዝርዝር እንደተመለከተው በ2007 በጀት ዓመት ሂሳቦች ላይ በተደረገው ኦዲት  የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ፣የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የገቢ ሂሳብና ለግል ጥቅም የዋለ፣ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ካለፉት ዓመታት የተሻለ  ቢሆንም በጥሬ ገንዘብ ጉድለት መጠን፣ ስርዓቱን ባልተከለተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ፣ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ ፣ማስረጃ ያልቀረበለት እና ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ የግኝቱ ሁኔታ እየጨመረ መሄዱን መረጃው ያሳያል፡፡

   በጥቅሉ ከ2003 እስከ 2007 ያሉት 5 በጀት ዓመታት ሂደቱ ሲገመገም በተወሰኑት ግኝቶች ላይ መሻሻል ቢታይም በአንዳንዶች ግኝቶች ላይ መሻሻል አልታየም ማለት ይቻላል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው በግራፍ ቀርቧል፡፡




**ጥሬ ገንዘብን በተመለከተ፤**

- የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,179,036.91 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀትሞ ገንዘብ ያገኘች ብር 121,994.23 በጉድለት ተገኝቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ17 መ/ቤት ብር 9,434,520.85 የሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ4 መ/ቤት በማነስ ብር 1,120,576.43 ተስተውሏል፡፡
- 73 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2007 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

**የገቢ ሂሣብን በተመለከተ፤**

- የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 249 መ/ቤቶች ውስጥ በ69 መ/ቤቶች ብር 59,328,259.60 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ73 (35.43%) መ/ቤቶች ብር 27,435,531.20 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት፤**

- የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ94 መ/ቤቶች ብር 828,281,282.42 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡
- የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ 4 መ/ቤቶች ብር 12,320,690.78 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቸ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡
- የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ67 መ/ቤቶች ብር 537,949,080.04 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

**የወጪ ሂሳብን በሚመለከት፤**

- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ11 መ/ቤቶች ብር 20,738,029.49 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ154 (74.75%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 13917929.12 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡
- ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ44 (21.35%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 45,059,727.70 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ማንኛውም □ኦ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባ ይህን በመተላለአ በ87 (42.23%) መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 24,831,883.94 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □ኦ□ ተ□□ሞና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ34(6%) መ/ቤቶች ብር 55,072,281.07 ተገኝቷል፡፡
- የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ166/80.58%/ መ/ቤቶች ብር 126,923,643.06 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

**የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት፤**

- የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ49 መ/ቤቶች ብር 64,188,419.24 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

**የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ፤**

- የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 206 መ/ቤቶች መካከል በ106(51.46%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

## የማሻሻያ አስተያየት፤

በዚህ ዓመት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ሀብቶችን አመራር ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶችን እናቀርባለን፣

**በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ስለማስፈለጉ**

ከግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

**የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤**

በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

**የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤**

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቱቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

**በየደረጃው ያሉ የህዝብ ምክር ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ክትትል ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡**

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጪ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

በሌላ በኩል ባለፈው ዓመትም ቀርቦ መፍትሔ ያላገኘውን ልማቱ የፈጠራቸው አዳዲስ መ/ቤቶችን በተመለከተ፤ መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው በመጨመሩ ምክንያት በታሰበው መሠረት በቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ

አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ለዚህም ምክንያቱ በጀታቸው በተነጻጻሪ ደረጃ አነስተኛ ቢሆንም እንደ ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎችና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ያሉ መ/ቤቶች ሂሣባቸውን ራሳቸውን ችለው ስለሚያንቀሳቅሱና እንደ አንድ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ስለሚቆጠሩ የኦዲት ተደራጊውን መ/ቤት ቁጥር እየጨመሩት ይገኛሉ ፡፡

በመሆኑም ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ያቀረብነው ተጨባጭ መፍትሄ ያላገኘው፡-

- በጀታቸውን ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚይዝላቸው በየዓመቱ ቁጥራቸው እያደረ የመጣው ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎችን የሂሣብ እንቅስቃሴ አማክሎ የሚከታተል በየወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በፑል ተደራጅተው የጋራ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ቢኖር፣
- በጀታቸውን ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሚይዝላቸው የአካል ተሃድሶ ማዕከላት የሂሳብ እንቅስቃሴ ለቢሮው ሪፖርት ሲያቀርቡ የሂሣብ ማስረጃዎችንም የሚያስረክቡበት ሁኔታ ቢመቻች፣-

- በጀታቸውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚይዝላቸው በዞንና በወረዳ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሂሣብ እንቅስቃሴ አመደበኛ ስራቸው ላይ ተጽዕኖ በማያመጣ መልኩ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል በኩል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ ቢኖር፣
- በጀታቸውን የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የሚይዝላቸው ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

ሌላው የኦዲት ተደራሽነትና ጥራት እንዲሁም የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ልምድ ያለው ሠራተኛ ፍልሰትን ለመቀነስ ከሌሎች አቻ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ክፍያ ጋር በማነጻጸር በጥናት የቀረበው የጥቅማ ጥቅም ማሻሻያ ጥያቄ ተግባራዊ ምላሽ ቢሰጠው መንግስት ለዚህ ክፍያ ከሚያወጣው ወጪ በእጥፍ ህዝብና መንግስት ከኦዲት ሙያው ተጠቃሚ እንደሚሆን እምነቴን እየገለጽኩ!! በቅርቡ ያቀረብነው የማሻሻያ ጥያቄ አውንታዊ ምላሽ የማይሰጠው ከሆነ ግን ልምድ ያለው ባለሙያ እየለቀቀ በትኩ የኦዲት ሙያ ልምድ በሌላቸው አዳዲስ ሰራተኞች እየተተካ በመሆኑ የክህሎት ሽግግር እና የስራ ጥራት ችግር እየተፈጠረ በህብረተሰቡ ላይም የመልካም አስተዳደር ችግር በአግባቡ እንዳይፈታ የሚያደርግና የመ/ቤቱ ራዕይና ተልኮ የሆነውን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መስፈንን የሚፈታተነው ተግባር እንደሚሆን ከወዲሁ አሳስባለሁ!!

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመስግናለሁ!!